# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 315 ሐምሌ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# የልበ ብርሃኖቹ-ተጨማሪ ብርሃን

**ተስፋ ፈሩ**

በቀዳማዊት እመቤት ጽህፈት ቤት አስተባባሪነት የተገነባው ብርሃን የአይነስውራን አዳሪ ትምህርት ቤት ግንቦት 11 ቀን 2016 ዓ.ም መመረቁ ይታወሳል። ቀዳማዊት እመቤቷ ለትምህርት ቤቱ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ሲያስቀምጡ፤ ትምህርት ቤቱ አይነ ስውራን ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙ በሚያስችል መልኩ ይገነባል ብለው ነበር። ቃላቸው በተግባር ተተርጉሟል።

እንደተባለው ትምህርት ቤቱ ለአይነስውራን ምቹ ሆኖ በከፍተኛ የጥራት ደረጃ ተገንብቷል። ዘመኑ በደረሰበት ቴክኖሎጂ ደረጃ የሚገኙ መሠረተ ልማቶች እንዲኖሩት ተደርጓል። ህንጻዎቹ ከአካባቢው ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ እርስ በርስ እንዲናበቡ ሆነው በድንቅ አቋቋም ይታያሉ። ምድረ ጊቢው በእጽዋትና አበቦች የተሞላ አረንጓዴ ነው። ለመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችም በሙሉ ተሟልተውለታል። ምን አለፋችሁ ተቋሙ አነስተኛ ጊቢ ከመሆኑ በቀር የአንድ ዩኒቨርሲቲን ቅርጽ የያዘ ነው።

በቀጣይ የአፍሪካ የአይነስውራን ተማሪዎች የልህቀት ማዕከል

የልበ ብርሃኖቹ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ወንዳየው ውቤ

# ጽዱ ኢትዮጵያ በ50 ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ ከተጀመረ አንስቶ አስካሁን በ50 ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ

ጽዱ ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በኦሮሚያ ክልል በተጠናቀቀው በጀት ዓመት፡-

## - ከ123 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ተሰብስቧል
## - ለ3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**ማርቆስ በላይ**

አዳማ፡- ኦሮሚያ ክልል በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ123 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡንና 3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን ርዕሰ መስተዳድሩ ገለጹ። በኢንቨስትመንት ዘርፍም 148 ቢሊዮን ካፒታል ላስመዘገቡ ፕሮጀክቶች ፈቃድ ተሰጥቷል ተብሏል።

የጨፌ ኦሮሚያ 6ኛ የሥራ ዘመን 3ኛ ዓመት 7ኛ መደበኛ ጉባዔ በአዳማ ከተማ እየተካሄደ ይገኛል።

የበጀት ዓመቱን አፈጻጸምና የቀጣይ በጀት ዓመት ዕቅድን ለጉባዔው ያቀረቡት ርዕሰ መስተዳድር ሽመልስ አብዲሳ እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት በርካታ ስኬቶች ተመዝግበዋል። ስኬቶቹ የሕዝቡን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ያረጋገጡ ናቸው።

ገቢን ለማሳደግ በበጀት ዓመቱ በተከናወኑ ተግባራት ከ123 ነጥብ 15 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን የገለጹት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በመደበኛ ገቢ 87 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በመዘጋጃ ቤት 22 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብርና ከውስጥ ገቢ 13 ነጥብ 06 ቢሊዮን ብር ተሰብስቧል ብለዋል።

የክልሉን የመንገድ ሽፋን ከ61 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ ማሳደግ መቻሉን የገለጹት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የክልሉ መንግሥት የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

በኦሮሚያ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የቅዱስ ጳውሎስ የካንሰር ህክምና ማዕከል አገልግሎት መስጠት ሊጀምር ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የካንሰር ህክምና ማዕከሉ ከአንድ ዓመት በአነሰ ጊዜ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወደ አገልግሎት ለማስገባት እየተሠራ መሆኑን የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ አስታወቀ። የማዕከሉ የሕንፃ ግንባታ 95

የቅዱስ ጳውሎስ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ወርቁ ጋቸና (ዶ/ር)



አቶ ሰለሞን ሙሉጌታ

## ሥልጠናው በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ በዓለም ተወዳዳሪ ፕሮጀክቶች እንዲሠሩ የሚያደርግ ነው

አዲስ አበባ፡- የክረምት ሥልጠናው ወጣቶች በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ችግር ፈቺና በዓለም ተወዳዳሪ ፕሮጀክቶችን እንዲሠሩ የሚያደርግ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ዶ/ር) አስታወቁ።

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የኤ.አይ ሰመር ካምፕ 2024 ሥልጠና መርሃ ግብር በትናንትናው እለት በሳይንስ ሙዚየም አስጀምሯል።

በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ዶ/ር) እንደገለፁት፤ የክረምት ሥልጠናው የኢትዮጵያ ወጣቶች በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ችግር ፈቺና በዓለም ተወዳዳሪ የሆኑ ፕሮጀክቶችን እንዲሠሩ ማብቃት የሚያስችል ነው።

የዓለም ሀገራት የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ እምቅ አቅምን በመረዳት በትኩረት እየሠሩበት ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኢትዮጵያም በዘርፉ ትኩረት ሰጥታ በመሥራት ጥሩ ውጤት እያስመዘገበች መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የኤ.አይ ሰመር ካምፕ ሥልጠና መርሃ ግብር የመደበኛ ትምህርት እንደተጠናቀቀ በየዓመቱ የሚሰጥ ሲሆን የዘንድሮው ለሶስተኛ ጊዜ ነው።

ሥልጠናው በመላ ሀገሪቱ ላሉ ተማሪዎች ለመስጠት ታስቦ ከሶስት ሺህ በላይ ተማሪዎች ምዝገባ ማካሄዳቸውን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ዘንድሮ 200 ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማሠልጠን ዝግጅት ተጠናቋል ብለዋል።


በዓለም ላይ በፍጥነት እያደገ የመጣውን የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ የሚመጥን የሰው ሃይል ለማፍራት በታዳጊዎች ላይ መሥራት ያስፈልጋል ያሉት ወርቁ (ዶ/ር)፤ በኢንስቲትዩቱ ሠልጣኞች ከሥልጠናው በኋላ ብቁ የምርምር ውጤቶችን ማበርከት እንዲችሉ የሚያደርጋቸው ግብዓት ተሟልቶላቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

የቴክኖሎጂ ባለሙያው አቶ ሰለሞን ሙሉጌታ በበኩላቸው አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ በዓለም ላይ በጣም ትልቅና እየተቀጣጠለ ያለ የአራተኛው የቴክኖሎጂ አብዮት ነው። በዚህ አቢዮት መሳተፍም ምርጫ ሳይሆን ግዴታ መሆኑን ገልጸዋል።

በዓለም ላይ በተለይም በአሁኑ ዘመን ታላቅ አብዮት የሆነውን የሰው ሰራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ለበጎ የምንጠቀምበት መሆን ይገባል ያሉት አቶ ሰለሞን ፤ ተማሪዎችም ወደ ክረምት ሥልጠናው ግብተው ያገኙትን እውቀት ተግባር ላይ እንዲያውሉ የወላጆች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ተናግረዋል።

# በክልሉ ከሌማት ትሩፋት ከ3 ነጥብ 4 ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት ምርት ተገኝቷል

ማህሌት ብዙነህ



አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በ2016 በጀት ዓመት ከሌማት ትሩፋት ከ3 ነጥብ 4 ቢሊዮን ሊትር በላይ ወተት ምርት ማግኘት መቻሉን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

በኦሮሚያ ግቢርና ቢሮ የወተት ሀብት ልማት ባለሙያ እና የሌማት ትሩፋት አስተባባሪ ተወካይ አቶ ጎሞሮ ዴሬሳ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ክልሉ በሌማት ትሩፋት የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሰፊ ሥራ ተሠርቷል። በዚህም በበጀት ዓመቱ 3 ነጥብ 36 ቢሊዮን ሊትር የወተት ምርት ለማምረት ታቅዶ 3 ነጥብ 492 ቢሊዮን ሊትር ማምረት ተችሏል።

በበጀት ዓመቱ በ4 ሺህ 277 የወተት መንደሮች ከ513 ሺህ 240 በላይ ህብረተሰቦች ተሳትፈዋል ያሉት ኃላፊው፤ 319 ሺህ 539 ጥጆች የተወለዱ ሲሆን ከአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን በላይ ላሞችን የማዳቀል ሥራ የተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል።

አቶ ጎሞሮ እንደገለጹት፤ የወተት ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል የወተት ላሞች እንክብካቤ እና ዝርያን የማሻሻል፣ የወተት ጥራት ለመጠበቅ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ እና የተደራጁ የወተት ማህበራት የገበያ ትስስር የመፍጠር ሥራ ተሠርቷል።

በዶሮ ልማት ሥራ ከ561 ሺህ 200 በላይ ነዋሪዎችን በማሳተፍ 104 ሺህ 779 ቶን በላይ የዶሮ ሥራ እንዲሁም ሁለት ነጥብ ሰባት ቢሊዮን በላይ የእንቁላል ምርት ማግኘት መቻሉን አያይዘው ገልጸዋል።

ከ53 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን በላይ የአንድ ቀን ጫጩት ማቅረብ የተቻለ መሆኑን ጠቁመው፤ ወጣቶችና ሴቶች በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው የአንድ ቀን ጫጩቶችና ቄብ ዶሮዎችን እንዲያራቡ በማድረግ ከፍተኛ የእንቁላል ምርት እንዲመረት ማድረግ የተቻለ መሆኑን ገልጸዋል።

እንዲሁም በከተማ ላይ ዶሮ እርባታ የሚያገለግሉ ሼዶችን በብዛት በማሠራትና ወደ ሥራ እንዲገቡ የተደረገ መሆኑንም አቶ ጎሞሮ ተናግረዋል።

በተጨማሪም በክልሉ በሚሠራው የሌማት ትሩፋት ሥራ 117 ሺህ 862 ቶን የማር ምርት የተገኘ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዚህም 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ንብ ቀፎ የቀረበ መሆኑን አስታውቀዋል።

በዓሣ ልማት ሥራም 690 ሺህ 757 ኩንታል የዓሳ ጫጩቶች በማቅረብ በአጠቃላይ 25 ሺህ 886 ቶን የዓሳ ምርት ተገኝቷል ብለዋል።

ለዚህ ዓሳ ልማት ሥራም አርሶ አደሮችን የዓሳ ኩሬ እንዲሠሩ የማድረግ ፣የዓሳ ጫጩቶች በኩሬዎችና ሀይቆች የመጨመር፣ የተሻሻሉ የዓሳ ጫጩቶች የማምረት እንዲሁም በሀይቆች ላይ የሚሠሩ ማህበራት በማደራጀት የዓሳ ምርት እንዲያመርቱ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ሱሉ ገልጸዋል።


እየጨመረ ለመጣው የእንስሳት ምርት የገበያ ትስስሩ አለመመጣጠን እና በቅንጅት መሥራት ላይ ደካማ ጎኖች የሚስተዋሉ መሆኑን አቶ ጎሞሮ ገልጸው፤ ይህንንም ለመፍታት የአቅርቦት ገዥዎችን በማቀላጠፍ ለግዢው ከማቅረብ ጀምሮ የተለያዩ የመፍትሄ ሥራዎች ተሥርተዋል ብለዋል።

በከተማ ላይ የእንስሳት ልማት በዘመናዊና በተደራጀ እየተስፋፋ ማምጣቱ በዘርፉ ላይ የተስተዋለ ጠንካራ ጎኖች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ይህም ለገቢ ምንጭነት፣ የምግብ ዋስትናና ሥርዓተ ምግብን ለማሻሻል እና በከፍተኛ የሥራ ዕድል ፈጠራ የሕዝባችንን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

# ሁለት ትውልድ፣ አንድ ተልዕኮ

ሳሙኤል ወንደሰን



አቶ ቶማስ ኃይሌ



ተማሪ ሲዲያ ኃይሌ

ዜና ሐተታ

በሰው ሕይወት እና ንብረት ላይ የሚደርሰውን ትራፊክ አደጋ መከላከል የጋራ ኃላፊነት ነው። በተለይ ህፃናት አስፋልት ሲሻገሩ ሲታይ ደግሞ የትራፊክ አደጋ ሁሉንም የሚያሳስብ ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ አባት አቶ ቶማስ ኃይሌ እና ልጅ ሊዲያ ኃይሌን ለበጎ ፈቃድ አነሳስቷል።

በየደቂቃው እግረኛውን እንዲህ አድርግ፣ አታድርግ እያሉ ከመናገር ባለፈ እግረኛውን በእጅ ገድቦ መያዝ፣ ቁም ከተባለበት የመንገድ አካፋይ ወጥቶ የእግረኛ ማቋረጫ መንገዱ ላይ የቆመውን ሰቦ ማስወጣት፣ መኪና እያለፈ ዘሎ የሚገባውን ጎትቶ ማውጣት፣ በሃሳብ ሆኖ አስፋልት ላይ መሆኑን የረሳውን እንዲሁም ሞባይሉን እያነጋገረ መኪና መንገድ መሀል የሚቆመውን ሃይ ማለት ለአባትና ልጅ የክረምት ሥራቸው ነው።

አቶ ቶማስ ኃይሌ እና ልጁ ሊዲያ ኃይሌን የሰውና የመኪና ትራፊክ ፍሰት በእጅጉ ከሚበዛባቸው ሥፍራዎች አንዱ በሆነው ፒያሳ እግረኞችን በመንገደኛ ማቋረጫ ለማሻገር ከሰዓት ከአሥር ሰዓት እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ድረስ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲሰጡ አይተናቸዋል።

አቶ ቶማስ ኃይሌ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩት በንግድ ሥራ ነው። በሚሠሩት ሥራ ገቢ ለማግኘት የግዴታ በሥራ ቦታቸው ላይ መገኘት እንዳለባቸው ተናግረዋል። “በክረምት ለአንድ ሰዓትና ለሁለት ሰዓት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራ እሠራለሁ።” ይላሉ አቶ ቶማስ።

በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ላይ መሰማራት የጀመርኩት 2010 ዓ.ም ላይ ነው የሚሉት አቶ ቶማስ፤ በክረምት የትራፊክ ሥራዎችን ማስተባበር፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስ፣ አካባቢ ማጽዳት፣ ችግኝ መትከልና መሰል ሥራዎችን በበጎ ፈቃድ እንደሚሠሩ ተናግረዋል።

እያንዳንዱ ሰው ባለችው ጊዜ ለ30 ደቂቃ የበጎ ፍቃድ ሥራ ቢሠራ እንደሀገር ያሉብንን በርካታ ችግሮች በጋራ መፍታት ይቻላል የሚሉት አቶ ቶማስ፤ “ልጆቼ በበጎ ፈቃድ ተነሳስተው የበጎ ፈቃድ ሥራዎችን እንዲሠሩና ስሜት እንዲኖራቸው እፈልጋለሁ” ነው ያሉት።

ይህም ልጆቻቸው ጥሩ ሥነ ምግባር ያላቸው፣ በትምህርታቸውና በሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል። በዚህም “ሀገር ተረካቢ ትውልድ መፍጠር እንችላለን” ይላሉ።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ደመወዝ የማያስከፍል ቢሆንም በሀገሪቱ ሰላምና ፍቅር እንዲኖር በማድረግ በትውልድ ላይ መልካም ስብዕና እንዲገነባ ያደርጋል ያሉት አቶ ቶማስ፤ ጊዜዎን፣ ጉልበትዎን እና ምናልባትም ሀብቶትን መለገስ፣ ልክ እንደአገልግሎቱ ተጠቃሚ አገልጋዩንም የሚክስ ህሊናዊ እርካታ ያለው መሆኑን ገልጸዋል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አዳዲስ ሰዎችን ለመገናኘት እና ብሎም ማህበረሰብን ለመገንባት ይረዳል። ስለ ሌሎች የሕይወት መንገድ እውቀትና ግንዛቤ እንድናገኝ፣ ዓላማ እንዲኖረን፣ ደስተኛ እንድንሆን፣ ሙያን ለማጎልበት እና ሌሎች በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉትም ጠቅሰዋል።

ተማሪ ሊዲያ ኃይሌ በበኩሏ፤ በዘንድሮ ክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ከመኪና መንገድ እግረኛውን ማስወጣቱና ፈር እንዲይዘ የማድረግ ሥራን እያከናወነች ነው። በዚህም ምን አገባሽ? ብሞት ብኖር አንቺን ምን ይመለከትሻል? የሚሉ ብዙ ናቸው ትላለች።

እግረኛው እንደ አጠቃላይ ሲታይም ደንቡን አክብሮ ከሚንቀሳቀሰው ይልቅ የሚያስቸግረውና ደንብ የሚጥሰው ይበዛል የምትለው ተማሪ ሊዲያ፤ “አባቴ በብዙ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ላይ ይሳተፋል። ይህም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራዎችን እንዳከናውን ተነሳሽነት ፈጥሮብኛል” ብላለች።

በክረምትም ሆነ በበጋ አቅመ ደካሞችንና ህጻናትን መደገፍ፣ በሀገር ልማት ላይ አስተዋጽኦ ማበርከት ከአንድ ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ተግባር ነው። ይህን ተግባር በማጠናከር የሚጠበቅባትን ኃላፊነት ለመወጣት ሁሌም ዝግጁ መሆኗን ተናግራለች።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን የምታከናውነው ትምህርቷን በማይጋጭ መልኩ መሆኑን ገልጻ፤ በጎ ፈቃደኝነት በራስ ተነሳሽነት የሚሠራና የህሊና እርካታ የሚያስገኝ ተግባር ነው። በጎነት ለራስ ስንቅ ነው። በዚህ በጎ ተግባር ላይ በመሳተፌ ደስታ ተሰምቶኛል ነው ያለችው።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጊዜ አይሻማም። የሚፈልገው ልብና ተነሳሽነት ብቻ ነው። ስለዚህ ተማሪዎች በተለይ በክረምት ወቅት የሚሠሩ ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ጠይቃለች። የዚህም ክፍያው የህሊና እርካታና ሰላም መሆኑን ገልፃለች።

በቤተልሔም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከአሥረኛ ክፍል ወደ አሥራ አንደኛ ክፍል እንደተዘዋወረች እና የትራፊክ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት ከአውቶብስ ተራ ፒያሳ ድረስ እንደምትመጣም ተናግራለች።

አቶ ቶማስ ኃይሌ እና ተማሪ ሊዲያ ኃይሌ የበጎ ፈቃደኝነት መንፈስ በምሳሌነት ያሳያሉ። ለትራፊክ ደህንነት ያላቸው ቁርጠኝነት ደንቦችን በመከተል ብቻ አይደለም፤ የበለጠ ጠንካራ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ በጋራ መገንባት ነው።

ታሪካቸው ያነሳሳናል። ይህም በአካባቢያችን በጎ ተጽዕኖ ለመፍጠር ጊዜያችንን እና ተሰጥኦአችንን እንዴት ማበርከት እንደምንችል ለማሰብ ያስችላል። እንደ በጎ ፈቃደኝነት ያሉ ተግባራትን የለውጥ ውጤት ለመፍጠር ያላቸው ኃይል ከፍተኛ ነው።



# በዞኑ ከ15 ሺህ ሔክታር በላይ መሬት ላይ ፍራፍሬ ለምቷል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በስልጤ ዞን ከ15 ሺህ ሔክታር በላይ መሬት ላይ የተለያዩ ፍራፍሬዎች መልማታቸውን የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ።

የስልጤ ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ ሙርሰል አማን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዞኑ ከፍተኛ የሆነ ፍራፍሬ ማምረት የሚያስችል አቅም አለ። በ2016 ዓ.ም ከ15 ሺህ 726 ሔክታር መሬት ላይ የተለያዩ ፍራፍሬዎች ለምተዋል።

በዞኑ ፍራፍሬን ለማምረት የሚያመች የተፈጥሮ ሀብት ቢኖርም ምቹ ሁኔታውን በስፋት የመጠቀም ልምዱ አነስተኛ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ሙርሰል፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የፍራፍሬን ልማት ሥራ በስፋት እየተተገበረ ይገኛል ብለዋል። ዞኑም ፍራፍሬን ለገበያ ለማቅረብ በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል።

የፍራፍሬ ምርት እየለማበት ከሚገኘው ከ15 ሺህ 726 ሔክታር መሬት ውስጥ ሦስት ሺህ 786 ነጥብ 72 ሔክታር የሚሆነው መሬት ምርት ለመስጠት መድረሱን ገልጸዋል።

እስካሁን በዞኑ 994 ሺህ 870 ነጥብ 25 ኩንታል የፍራፍሬ ምርት መሰብሰቡን ጠቁመው፤ ከተሰበሰበው ምርት ውስጥ 397 ሺህ 948 ኩንታል የፍራፍሬ ምርት ለገበያ መቅረቡን አብራርተዋል።

የፍራፍሬ ልማቱን ለማስፋፋት ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ሰብሎች ላይ ተግባራዊ ይደረግ የነበረውን የክላስተር አስተራረስ ዘዴ ተግባራዊ መደረጉን አንስተው፤ ችግኞች በተደራጀ መልኩ በጥራትና በብዛት እየተዘጋጁ ይገኛል ብለዋል።

በዞኑ በኩታ ገጠም ለሚከናወነው የፍራፍሬ ልማትም በየዓመቱ ከሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ የተለያዩ የፍራፍሬ ችግኞች እንደሚዘጋጁ ገልጸዋል።

በዞኑ አርሶ አደሮች የተመረጡ የፍራፍሬ አይነቶች እንዲያለሙ እየተሠራ መሆኑን ተናግረው፤ ከ2014 እስከ 2016 ዓ.ም ባለው ጊዜም አፕል፣ ሙዝ እና የፓፓያ ፍራፍሬዎችን የሚያለሙ 90 የፍራፍሬ መንደሮች ተፈጥረዋል ሲሉ አስረድተዋል።

በእያንዳንዱ መንደር አንድ መቶ አርሶ አደሮችን በማሳተፍ እያንዳንዳቸው መቶ የፍራፍሬ ችግኞች እንዲተክሉ መደረጉን አመላክተዋል።

በ90 መንደሮችም አንድ ነጥብ 15 ሚሊዮን የፍራፍሬ ችግኞች መትከል እንደተቻለ አስታውቀው፤ ከተተከሉት ውስጥ የሙዝና የፓፓያ ምርት በመሰብሰብ ላይ እንደሚገኝ አቶ ሙርሰል ተናግረዋል።

ኃላፊው እንዳስታወቁት፤ በፍራፍሬ ልማቱ ከሌሎች አካባቢዎች ጋር የገበያ ትስስር መፍጠር ተችሏል። በርካታ አርሶ አደሮች ለአጎራባች አካባቢዎችና ለማዕከላዊ ገበያ በማቅረብ የተሻለ ገቢ እያገኙ ነው።

# ተስፋ ድርጅት በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ያሠለጠናቸውን 388 ሠልጣኞችን አስመረቀ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ተስፋ ድርጅት የቴክኒክና ሙያ ተቋም በአራት የተለያዩ አጫጭር ሥልጠና ዘርፍ ያሠለጠናቸውን 388 ሠልጣኞች ከትናንት በስቲያ አስመርቋል።

ሥልጠናው በኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፣ በምግብ ዝግጅት፣ በልብስ ስፌት እንዲሁም በመኪና ጥገና ዘርፎች ሲሆን ለተከታታይ ስድስት ወር ሥልጠና መውሰዳቸውን በመድረኩ ተገልጿል።

የተስፋ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጥላሁን አበጋዝ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ሥልጠናው ለዜጎች የሥራ እድል ከመፍጠር ጎን ለጎን ኢንዱስትሪው የሚፈልገው የሰው ኃይል በማብቃት ረገድ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው።

ተመራቂዎቹ በተለያዩ የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ለስድስት ወር ሥልጠና ወስደዋል ያሉት አቶ ጥላሁን፤ ሠልጣኞች በሥልጠና ካገኙት እውቀት በተጨማሪ የራሳቸው የነቃ ተሳትፎና ክህሎት በመጨመር የተሻለ ሥራ መሥራት አለባቸው ብለዋል።

ድርጅቱ ከአጸደ ህጻናት ጀምሮ እስከ ኮሌጆች ድረስ ሥልጠና መስጠት እንዲሁም ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ እንዲቀላቀሉ የተለያዩ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ጥላሁን ገለጻ፤ ሥልጠናው በተለያዩ ሀገር በቀልና የውጭ ሀገራት ግብረ ሰናይ አጋር ድርጅቶች የተሰጠ ነው።

የተስፋ ድርጅት ምክትል ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍሬው ደሳለኝ በበኩላቸው፤ ድርጅቱ 1971 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ ማህበረሰብ አቀፍ ሥራዎች እየሠራ ይገኛል ያሉ ሲሆን ድርጅቱ ላለፉት 35 ዓመታት በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ሠልጣኞችን አስመርቋል ብለዋል።

አቶ ፍሬው አክለውም፤ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናው በአዲስ አበባ፣ በጋምቤላ እንዲሁም በደሴ፣ እያሠለጠነ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።



ድርጅቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሰባት ትምህርት ቤቶች ከአምስት ሺህ ህጻናት በላይ የትምህርት ምገባ እያካሄደ ይገኛል ያሉት አቶ ፍሬው፣ በተጨማሪም ደብረብርሃን በመጠለያ ጣቢያ ለሚገኙ ለሶስት ሺህ ህጻናት የምግብ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

ድርጅቱ አነስተኛ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍል መሠረት በማድረግ ዘርፈ ብዙ የልማት ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል ያሉት ደግሞ በተስፋ ድርጅት የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ አቶ ምንተስኖት ካሳዬ ናቸው።

ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በመስጠት በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን የሙያ ባለቤት በማድረግ ወደ ሥራ እያስገባ ዘላቂ በሆነ መንገድ ራሳቸውን ችለው ለሌሎች የሚተርፉ ዜጎችን መፍጠር ችሏልም ነው ያሉት።

ከመደበኛ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናው በተጨማሪ የሥነ-ዜጋ፣ ሥነ-ምግባር የህይወት ክህሎት እንዲሁም የንግድ ሥራ ክህሎት እያሠለጠነ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመተባበር ከስደት ተመላሽና ጉዳት ለደረሰባቸው 102 ወጣቶች በማሠልጠንና የሥራ ስምሪት በማድረግ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረጉንም ነው የገለጹት።

ተመራቂዎቹ የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸውና ወላጅ አልባ የሆኑ ከአጸደ ህጻናት ጀምሮ በመመልመል በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ያሠለጠናቸው መሆኑ ተገልጿል።

# የጉራጌ ልማትና ባህል ማህበር 12ኛ ዙር የችግኝ ተከሳ መርሃ ግብር አካሄደ

**አማን ረሺድ**

እኖር ኤነር፡- የጉራጌ ልማትና ባህል ማህበር በጉራጌ ዞን እኖር ኤነር መገር ወረዳ የ12ኛ ዙር የችግኝ ተከላ መርሃግብር አካሂዷል።

ማኅበሩ መርሃ ግብሩን ያከናወነው “ጉዞ ወደ አረንጓዴ ልማት” በሚል መሪ ሃሳብ ነው።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንደሻው ጣሰው በመርሃ ግብሩ እንደገለጹት፤ በመርሃ ግብሩ የሚተከለው ችግኝ ብቻ ሳይሆን ሰላም፣ ፍቅርና አብሮነትን በመሆኑ ሕዝቡ በአንድነት በችግኝ ተከላው ዐሻራውን ሊያኖር ይገባል።

ክልሉ በግብርና ዘርፍ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ አቅዶ እየሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ እንዳሻው፤ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ኢትዮጵያን ከተረጂነት ለማውጣት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል። ለዚህም አረንጓዴ ዐሻራ ሚናው ከፍተኛ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ እንደሻው ገለጻ፤ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀግብር እንደሀገር ከተረጅነት ለመውጣት እየተደረገ ላለው ጥረት፣ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥና የአየር ንብረትን ለመጠበቅ ያግዛል።

በሁሉም የልማት ሥራ የክልሉ ሕዝብ በንቃት ሊሳተፍ እንደሚገባ ገልጸው፤ የአረንጓዴ ዐሻራ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ የተተከሉ ችግኞችን በመንከባከብ የጽድቀት መጠናቸውን ማሳደግ ይገባል ብለዋል።

የጉራጌ ልማትና ባህል ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ



ሺሰማ ገብረሥላሴ በበኩላቸው፤ ማህበሩ የተራቆቱ አካባቢዎችን በደን ለመሸፈን ላለፉት 11 ዓመታት ሕዝቡንና አባላቱን በማስተባበር በርካታ ችግኞችን ተክሏል።

ማህበሩ በዘንድሮ የ12ኛ ዙር የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ከ20 ሺህ በላይ ሀገር በቀል ችግኞችን መትከሉን ገልጸዋል።

በሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ምክንያት ለሚያጋጥሙ አደጋዎች የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ መድረኮችን በማዘጋጀት ወገንተኝነቱን አሳይቷል ብለዋል።

ማህበሩ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትምህርት ቤት፣ ጤና ጣቢያ፣ የውሃ ተቋምና መሰል የመሠረተ ልማት ሥራ ሲሠራ መቆየቱን አስረድተዋል።

የጉራጌ ዞን ምክትል አስተዳዳሪና የግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ አበራ ወንድሙ በበኩላቸው፤ ህብረተሰቡ ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን ተንከባክቦ በማሳደግ ለውጤት በማብቃት ረገድ ተሳትፎውን በማጠናከር እንደ ሀገር የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት መረባረብ አለበት ብለዋል።

በክልሉ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በርካታ ችግኞች ተዘጋጅተው በአሁኑ ወቅት የተከላ ሥራው በተለያዩ ዞኖችና ከተሞች በመከናወን ላይ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ አርሶ አደሩ በዝናብ እጥረት ምክንያት ሲያጋጥመው የነበረውን ችግር መቅረፍ መቻሉን ገልጸዋል።

በችግኝ ተከላ መርሃግብሩ ላይ የፌዴራል፣ የክልል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የዞንና የወረዳ አመራሮች፣ የልማት ማህበሩ አጋሮች፣ ደጋፊዎች እንዲሁም የአካባቢው ነዋሪዎች ተሳትፈዋል።

በዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀግብር 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከት ታቅዶ ከሰኔ ወር ጀምሮ ተከላ መጀመሩን የሚታወስ ነው።

# የቅዱስ ጳውሎስ

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

በመቶ መጠናቀቁም ተገልጿል።

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ የካንሰር ህክምና ማዕከል ኃላፊና የካንሰር ህክምና ስፔሻሊስት መሀመድ ኢብራሂም (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የቅዱስ ጳውሎስ የካንሰር ህክምና ማዕከልን ከአንድ ዓመት በአነሰ ጊዜ ውስጥ አገልግሎት መስጠት እንዲጀምር ሰፊ ርብርብ እየተደረገ ነው።

ግንባታው በተለያዩ ችግሮች እና የግብዓት መወደድ ምክንያት ከስድስት ዓመታት በላይ መጓተቱን የጠቆሙት ዶክተር መሀመድ፤ አሁን 95 በመቶ የሚሆነው በማጠናቀቅ የኤሌክትሮ ሜካኒካል ገጠማ ላይ ይገኛል ብለዋል።

ሕንፃው ምድር ቤትን ሳይጨምር ስምንት ወለሎች እንዳሉትም ጠቁመዋል።

ከማሽን ግዢው ውጪ የአልጋና የሌሎች ቀላል አገልግሎት ችግሮችን ለመቅረፍ ከስድስት ወራት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ወደ አገልግሎት ማስገባት እንደሚቻል አብራርተዋል።

ዶክተር መሀመድ እንደገለጹት፤ በማዕከሉ አራት የጨረር ማሽኖች እና አንድ ኒኩላር ሜዲሲን የሚቀመጥባቸው አምስት ባንከሮች ተሠርተው ተጠናቀዋል። ጨረሩ በአካባቢው ጉዳት እንዳያስከትል የሕንፃ አሠራሩ ለየት ተደርጎ ተሠርቷል።

በቀጣይም የጨረር ማሽኖቹ ወደ ሀገር ውስጥ የማስገባትና በቦታቸው የማስቀመጥ ተግባር ለማከናወን የትኩረት አቅጣጫ መያዙንም ነው ዶክተር መሀመድ ያመላከቱት።

ማዕከሉ የካንሰር ታማሚ ወደ ውጭ ሀገር መሄድ ሳይጠበቅበት ሙሉ በሙሉ አገልግሎቱ እንዲያገኝ ከማድረግ ጎን ለጎን ሲጠናቀቅ በተለያየ ቦታ ይታከም የነበረውን የካንሰር ታካሚ በአንድ ቦታ በመሰብሰብ አገልግሎቱን እንዲያገኙ የማድረግ አቅም እንዳለውም ተናግረዋል።

በሀገሪቱ በአንድ ማዕከል አምስት ባንከር ያለው ትልቁና የመጀመሪያው የካንሰር ማዕከል መሆኑንም ነው ያብራሩት።

እንደ ዶክተር መሀመድ ገለጻ፤ ማዕከሉ አጠቃላይ 360 ተኝቶ መታከሚያ አልጋ አለው። በተጨማሪም ለካንሰር ህክምና የሚያገለግሉ ስድስት ደረጃቸውን የጠበቁ የቀዶ ሕክምና ክፍሎች አሉት።

ማዕከሉ በሀገሪቱ ከዚህ በፊት የማይሰጡ የካንሰር ህክምናዎች አካቷል ያሉት ኃላፊው፤ ሙሉ በሙሉ የጨረር ህክምና፣ ኒኩለር ሜዲሲን እንዲሁም የመቅኔ ንቅለ ተከላ ተጠቃሽ መሆናቸውን አስረድተዋል።

ማዕከሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ችግር በመቅረፍ ረገድ ትልቅ ድርሻ እንዳለው ጠቅሰው፤ በተለይ ከዚህ በፊት ያልነበሩ ህክምናዎች የሚያካትት በመሆኑ የሰው ሕይወት ከመታደጉም በላይ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጪን ማስቀረት የሚችል መሆኑን አስገንዝበዋል።

በተጨማሪም ማዕከሉ ዓለም የደረሰችበት የጨረር ህክምና ቴክኒክ ተግባራዊ ያደረገ በመሆኑ የካንሰር ታካሚዎች ሳይጉላሉ በቅርበት አገልግሎት የሚያገኙበት ነው ብለዋል።

ማሽኖቹ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቁ በመሆናቸው ማዕከሉ በተያዘለት ጊዜ ወደ አገልግሎት ለማስገባት የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍበት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።



ፎቶ ሐዲስ አብርሃ

# ጽዱ ኢትዮጵያ…

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

እንደሚገኝ የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በጤና ሚኒስቴር የዋሽና አካባቢ ጤና አስተባባሪና የህብረተሰብ ጤና ባለሙያ አቶ ወንዳየው ውቤ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ጽዱ ኢትዮጵያ በሀገር አቀፍ በ50 ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው።

በቀጣይም 200 ወረዳዎች በላይ ለመድረስ እየተሠራ ነው ያሉት አስተባባሪው፤ እስከ 2018 ዓ.ም ድረስ በሀገሪቱ ሁሉም ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ እቅድ መያዙን ተናግረዋል።

በተለይ የህብት አሰባሰብና ለህብረተሰቡ ግንዛበቤ ከመፍጠር አኳያ ሰፋፊ ሥራዎች መሠራታቸውንም ነው አስተባባሪው የጠቆሙት።

እንደ አቶ ወንዳየው ገለጻ፤ ጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ 65 በመቶ በሽታዎችን መከላከል ያስችላል። በመዲናዋ የጽዱ ኢትዮጵያና የኮሪደር ልማት ከተጀመረ ወዲህ ከጤና አጠባበቅ አንጻር ውጤት እያስገኘ ይገኛል።

ከዚህ በፊት በህንድ ‹‹ጽዱ ህንድ›› በሚል በተደረገ ንቅናቄ ህንድ ውጤታማ ሥራዎችን መሥራት ችላለች ያሉት ኃላፊው፤ ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት በተለይ ተቋማት በመሪነት ደረጃ ንቅናቄውን ማስቀጠል እንዳለባቸው አሳስበዋል።

ጽዱ ኢትዮጵያ ከተጀመረ በኋላ ከበርካታ አጋር አካላት ጋር ሲሠራ ቆይቷል ያሉት አቶ ወንዳየው፤ ለአብነትም ፕሮግራሙ በዘላቂነት እንዲመራና የሚፈልገው ውጤት ለማግኘት የዶክመንት፣ የእስትራቴጂ ሥራዎች ዝግጅት መከናወኑን እና ተግባራዊ ያደረጉ ወረዳዎች ግምገማ መደረጉን አብራርተዋል።

አቶ ወንዳየው አክለውም፤ ጽዱ ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ 222 ቢሊዮን ብር በላይ በጀት ያስፈልገዋል ያሉ ሲሆን በጀቱ ከመንግሥት፣ ከግል ተቋማት፣ ከአጋር አካላት እንዲሁም ከሕዝብ ተሳትፎ የሚሸፈን ነው ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ ከ100 በላይ መጸዳጃ ቤት ለመገንባት ከከተማ አስተዳደሩ ቦታ ለመውሰድ በእንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ይህም ከጤና አኳያ ከሚኖረው ከፍተኛ ጠቀሜታ ጎን ለጎን የዘላቂ ልማት ግብ እውን ለማድረግ የሚያግዝ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ጽዱ ኢትዮጵያ ከቆሻሻ የጸዳና አረንጓዴ ልምላሚ የተላበሰ አካባቢ በመፍጠር የሠለጠነና የነቃ ዜጋ ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑንም አቶ ወንዳየው ገልጸዋል።

የጽዱ ኢትዮጵያ ንቅናቄ የአገልግሎት ጥራት ከማምጣትና ለሁለንተናዊ እድገት የሚጫውተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ሁሉም ተቋማትና ዜጋ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

# በኦሮሚያ ክልል…

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

በተጠናቀቀው ዓመት 421 የጤና ተቋማት ግንባታ በማጠናቀቅ ለአገልግሎት ክፍት መደረጉን በመግለጽ፤ 673 ሺህ ዜጎች የተኝቶ ህክምና ማግኘታቸውን ተናግረዋል።

በንፁህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነት ከ2 ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን የገለጹት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በመንግሥት፣ በሕዝብና በልማታዊ ድርጅቶች 9 ሺህ 654 የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደ አገልግሎት መግባታቸውን አስረድተዋል።

የእናቶችና ህፃናት ሞትን ለመቀነስ፣ ወረርሽኞችን ለመከላከልና የመድሃኒት እጥረትን ለመፍታት መሠራቱን ጠቅሰው፤ የጤና ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን በተከናወኑ ተግባራት አበረታች ውጤት መመዝገቡን ገልፀዋል።

በትምህርት ቤቶች ተደራሽነት ላይ በተያዘው ዓመት 4 ሺህ 383 ቡኡረ ቦኑ ትምህርት ቤቶች በሕዝብ ተሳትፎ መገንባታቸውን በመግለጽ የቡኡረ ቦኑ ትምህርት ቤቶችን ቁጥር 15 ሺህ 225 ማድረስ መቻሉን ተናግረዋል።

በበጀት ዓመቱ 6 ሺህ 11 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ደረጃ ማሻሻል መቻሉን ገልጸው በተማሪዎች ምገባ 6.9 ሚሊዮን ተማሪዎች ተጠቃሚ መሆናቸውን አስረድተዋል።

በበጀት ዓመቱ 3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል ያሉት አቶ ሽመልስ፤ በበጀት ዓመቱ የተመዘገቡ ስኬቶችን አጠናክሮ በሚያስቀጥል እና ጉድለቶችን መሙላት በሚያስችል መልኩ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ መቀረፁን አመላክተዋል።

በኢንቨስትመንት 148 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ 3 ሺህ 757 ፕሮጀክቶች ውሳኔ ማግኘታቸውን ጠቅሰው ፕሮጀክቶቹ 599 ሺህ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር የሚችሉ መሆናቸውንም ተናግረዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የምግብና ሥነምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በግብርናው መስክ ትልቅ አብዮት መካሄዱንና ይህም ቀጣይነት እንደሚኖረው ገልጸዋል።

በ2016/17 የምርት ዘመን በመኸር እርሻ 10 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማልማት 337 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ መታቀዱን ጠቁመዋል።

በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በክልሉ 5 ነጥብ 4 ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል መታቀዱን ገልጸው፤ እስካሁን 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ችግኝ እንደተተከለ ተናግረዋል።

የጨፌ ኦሮሚያ መደበኛ ስብሰባ ዛሬም የሚቀጥል ሲሆን በተለያዩ አዋጆች እና ሹመቶች ላይ እንዲሁም የ2017 ረቂቅ በጀት ላይ በመወያየት ያጸድቃል ተብሎ ይጠበቃል።

# የልበ ብርሃኖቹ…

ከ 1ኛ ገፅ የዞረ

የመሆን ራዕይን የሰነቀው ብርሃን የአይነስውራን አዳሪ ትምህርት ቤት፣ በሀገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን በምስራቅ አፍሪካም በአይነቱ የተለየ ነው።

ትምህርት ቤቱ እጅግ የተዋቡ 24 የመማሪያ ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ በአንድ ክፍል ውስጥ 16 ተማሪዎች ብቻ ይማራሉ። በርካታ ኮምፒዩተሮችና የጆሮ ማዳመጫዎች ያሉትና በሚገባ የተዋቀረ ዲጂታል ቤተ መጽሐፍት ይዟል። በብሬል መጽሐፍት የተሞላ ሁለተኛ ቤተ መጽሐፍትም አለው። ተማሪዎች የተለያዩ የእጅ ሥራ ውጤቶችን የሚሠሩበት ሰፊና ምቹ ወርክሾፕ አካትቷል። 12 የመሮጫ ማሽኖችን ጨምሮ የተለያዩ የስፖርት መሥሪያ ማሽኖችና ቁሳቁሶች የተሟላለት ጂም አለው።

312 አልጋዎች ፍራሽ፣ አንሶላና ኮምፎርት ተሟልቶላቸው ተማሪዎችን እየጠበቁ ይገኛሉ። እያንዳንዱ መኝታ ክፍል የራሱ መታጠቢያና መጸዳጃ ቤት ተሟልቶለታል። ከሠራተኛ ቅጥር ጋር ተያይዞ ተማሪዎች በእያንዳንዱ ማደሪያ ክፍል ሞግዚት እንዲኖራቸው ታሳቢ ተደርጓል። ተማሪዎቹ ቀን እና ሌሊት በሁለት ፈረቃ እንቅስቃሴ ላይ እንዳይቸገሩ ሞግዚቶቹ ድጋፍ ያደርጉላቸዋል።

በዘመናዊ መሣሪያዎች የተሟላ ማብሰያ ክፍል ከሰፊ እና ንጹህ የመመገቢያ አዳራሽ ጋር አጣምሮ ይዟል። በፈረስ ኮቴ ቅርፅ የተሠራው ማብሰያና መመገቢያ ክፍሉም በአረንጓዴ እጽዋት አሸብርቋል። በቀኝ በኩል የተዘረጋው አዳራሽ በሴቶች ማደሪያ ህንጻ ትይዩ የሚገኝ በር ያለው ሲሆን፣ በግራ በኩል የሚገኘው ደግሞ ከወንዶች ማደሪያ ሕንጻ በቀጥታ የሚያስገባ በር አለው። ሁለቱ አዳራሾች መሀከል ላይ በሚገኘው ማብሰያና የተዘጋጁ ምግቦች ማቅረቢያ ቦታ የተገናኙ ናቸው።

አስገራሚ በሆነ ዲዛይን የተሰራ ለእንቅስቃሴ ምቹ የሆነ የህክምና መሣሪያዎችና መድኃኒቶች የተሟሉለት ክሊኒክ በተጠንቀቅ ቆሟል። ክሊንኩ 24 ሰዓት ስለሚሠራ ተረኛ ለሚሆኑ ሀኪሞች ሳሎን፣ ማብሰያ ቤት፣ ሁለት መኝታ ክፍል እና መታጠቢያ ቤት ከሙሉ የቤት ዕቃ ጋር የተሟሉለት ማረፊያ ተዘጋጅቶላቸዋል።

ትምህርት ቤቱ በአሁኑ ወቅት ዋና ርዕሰ መምህር እና ሶስት ምክትል ርዕሳነ መምህራን ተመድበውለት ለ2017 ዓ.ም. የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ዝግጅት እያደረገ ይገኛል።

የብርሃን የአይነስውራን አዳሪ ትምህርት ቤት ዋና ርዕሰ መምህር አቶ ተፈሪ ንጉሤ እንደሚናገሩት፤ የትምህርት ቤቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ፣ መዋቅራዊ አደረጃጀት እና መተዳደሪያ ደንብ ዝግጅቶች ተጠናቀዋል። የሰው ኃይል መዋቅሩ ጥናት ተጠናቆ ለሚመለከተው አካል ቀርቦ በማጽደቅ ሂደት ላይ ይገኛል። የቋቋሚያ አዋጁም በባለሙያዎች ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ተመርቷል።

ከትምህርት ቢሮ ጋር በመሆን የሰው ኃይል መመልመያ መስፈርት ተዘጋጅቷል፣ አሁን የሚቀረው መምህራንን እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ወደ ተቋሙ ማምጣት ነው። ትምህርት ቢሮን 80 መምህራን እንዲያሟላልን ጠይቀን የቅጥር ሂደት ተጀምሯል የሚሉት ርዕሰ መምህሩ፤ በቀጣይ ሁለት ሳምንታት ውስጥ የቅጥር ሂደቱ ተጠናቆ የተማሪዎች ቅበላ ሂደት ይጀመራል ተብሎ እንደሚጠበቅ ይገልጻሉ።

ትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን ከ11 ክልሎችና ከሁለት ከተማ አስተዳደሮች ለመቀበል ዝግጅት ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ የምልመላ ሂደቱ በየክልሉ ያሉ የአይነስውራን ተማሪዎች ቁጥር ተወስዶ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ በተሰጠ ኮታ እየተከናወነ እንደሚገኝ ይገልጻሉ። ትንሿ ኢትዮጵያ የምትታይበት ትምህርት ቤት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል ሲሉም ያክላሉ።

የተማሪዎች አገልግሎት ምክትል ርዕሰ መምህርቷ ወይዘሮ ዓለም ከበደ፤ ትምህርት ቤቱ ነሐሴ 15 ቀን 2016 ዓ.ም ተማሪዎችን መቀበል ይጀምራል። ለዚህም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ጋር በመሆን ተማሪዎችን ከአውቶብስ ተራ ጀምሮ ሳይንገላቱ ወደ ትምህርት ቤቱ የሚያደርሷቸው በጎ ፈቃደኞችን ከማዘጋጀት ጀምሮ ግብረኃይል ተዋቅሮ የቅበላ ሂደቱን ለማሳለጥ እየተሠራ ነው ይላሉ።

ተማሪዎችን ከተቀበልን በኋላ ከትምህርት ቤቱ ምድረ ጊቢ ጋር እንዲተዋወቁ የሚያስችል ሥልጠና ለመስጠት ዝግጅት አድርገናል። በዚህም በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች በጊቢው ተገኝተው ምድረ ጊቢውን እንዲረዱ በማድረግ ተማሪዎች ወደ ተቋሙ ሲገቡ የማላመድ ሥራ መሥራት የሚያስችላቸው አቅም ተፈጥሯል ሲሉም ያክላሉ።

የተማሪዎች መኝታ ክፍል በአግባቡ ተደራጅቶ ተስተካክሏል፤ ልብሳቸውን የሚያስቀምጡበት መሳቢያ፤ ጫማቸውን የሚያስቀምጡበት የጫማ መደርደሪያ እና አልባሳት ሁሉ ዝግጁ ሆነው ተማሪዎችን እየጠበቁ ነው ሲሉ ቅድመ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን የሚጠቁሙት ምክትል ርዕሰ መምህርቷ፤ “እዚህ ትምህርት ቤት መምጣት ዕድል ነው። አሁን ለሚቀበለው 312 ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ አይነስውራን ተማሪዎች ተቋሙን ለመቀላቀል ጠንክረው እንዲማሩ ትልቅ መነሳሳትን ይፈጥራል” ብለዋል።

የአካዳሚ ጉዳዮች ምክትል ርእሰ መምህሩ አቶ አባይ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ ወደተቋሙ የሚገቡ ተማሪዎች ተወዳደሪ የሆኑ ናቸው። እያንዳንዱ ክልል የራሱን መስፈርት በማውጣት ተማሪዎችን ለይቶ ልኮልናል። በዚህም ከ11 ክልሎች 383 የተማሪዎች ዝርዝር መጥቶልናል። የ9ኛ፣10ኛ፣11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተቀብለን ለማስተማር ዝግጅት አድርገናል። ከሌሎች ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች አንጻር እጥፍ ድርብ በሆነ መልኩ ግብዓት የተሟላለት ነው ይላሉ።

አቶ አባይ እንደሚናገሩት፤ በተማሪዎች ቅበላ ወቅት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ተሟልተዋል። የብሬል ወረቀት፣ የብሬል መጻፊያዎች፣ ዘመናዊ መነጽሮች፣ አልባሳት እና ጫማዎች በትምህር ቤቱ ስቶር ይገኛሉ።

የሰበታ አይነ ስውራን ትምህርት ቤት በአጼ ኃይለስላሴ ዘመን የተገነባ የመጀመሪያው የአይነ ስውራን ትምህርት ቤት ሲሆን፣ ብርሃን የአይነስውራን አዳሪ ትምህርት ቤት ከስድስት አስርት ዓመታት በኋላ የተገነባ ሁለተኛው በረከት ነው።

የትምህርት ቤቱ መሠረተ ድንጋይ ሲቀመጥ በሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙት ሎሬት የትነበርሽ ንጉሤ፤ ቀዳማዊት እመቤቷ ከቀዳማዊ ሃይለስላሴ ቀጥሎ የአይነ ስውራን ጉዳይ ይመለከተኛል በሚል ትምህርት ቤት የሚገነቡ ብቸኛ ሰው ናቸው ሲሉ አሞካሽተዋቸው ነበር።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩን ስኬት ወደ ላቀ አፈጻጸም ደረጃ ለማድረስ!

ኢትዮጵያ የዘንድሮውን የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር የችግኝ ተከላ እያካሄደች ትገኛለች። ሀገሪቱ በእዚህ ክረምት ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል አቅዳ ባለፈው ሰኔ ወር በይፋ ወደ ተከላው ገብታለች። የችግኝ ተከላውም በየክልሎቹና ከተማ አስተዳደሮቹ በተጠናከረ መልኩ እየተካሄደ ነው። ሰሞኑን የወጣ መረጃ እንዳመለከተውም፤ እስከ አሁን አራት ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል።

የዘንድሮው የችግኝ ተከላ የእስከአሁን አፈጻጸም፣ በችግኝ ተከላው ለመትከል ከታቀደው የችግኝ መጠን ከግማሽ በላይ መትከል መቻሉን ያመለክታል። የክረምቱ ወቅት ገና እንደመግባቱ የችግኝ ተከላው አፈጻጸም በጥሩ አፈጻጸምነት ሊያዝ የሚችል ነው። አፈጻጸሙ በዚህ ደረጃ ላይ ለመገኘቱ በርካታ ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል። ለችግኝ ተከላው አስቀድሞ የተደረገው በቂ ዝግጅት፣ ዝናቡ የሰጠ መሆኑ፣ ዜጎችን በችግኝ ተከላው በማስተባበር በኩል ጥሩ መሠራቱ የሚሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን ባለፉት ዓመታት በችግኝ ተከላው ያካበቱት ልምድ ለእዚህ ዓመቱ የችግኝ ተከላ አስተዋጽኦ አበርክቷል ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

እንደሚታወቀው፤ ኢትዮጵያ በመጀመሪያው ዙር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል አቅዳ 25 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ከዕቅድ በላይ ሠርታለች። በችግኝ ተከላውም 20 ሚሊዮን ዜጎቿን አሳትፋለች። በ2011 ዓ/ም በተጀመረው በዚህ የአረንጓዴ ዐሻራ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር እስከ አለፈው ዓመት ድረስ 32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል። በአንድ ጀንበር ለመትከል ከታቀደውም በላይ ሲተከል እንደነበርም ይታወቃል።

ዘንድሮ እስከ አሁን የተተከሉት ችግኞች ብዛት ሲታሰብ ይህ የመርሀ ግብሩ ያለፉት ዓመታት ትልቅ ስኬት በዘንድሮ የችግኝ ተከላ ከፍተኛ ተሞክሮ እንደሚያበረክት ይታመናል። ተሞክሮው በዚህ ዓመት የችግኝ ተከላም ያለፉትን ስኬታማ ተግባሮች መድገም እንደሚቻል ያመለክታል። ዜጎች ለችግኝ ተከላው በቀጣይም በስፋት የሚወጡባቸው ጊዜያት አሁንም ሰፊ ናቸው። እነዚህን ጊዜያት በአግባቡ በመጠቀም የችግኝ ተከላውን አስቀድሞ በማጠናቀቅ ስኬታማነቱን በሚገባ ማሳየት ይገባል።

ለብልህ አይነግሩም፤ ለአንበሳ አይመትሩም እንደሚባለው ኢትዮጵያውያን በችግኝ ተከላው ስማችሁ በደማቁ የተመዘገበ እንደመሆኑ በችግኝ ተከላው የሚያደርጉትን ርብርብ እንደሚያጠናክሩ ይጠበቃል። የችግኝ ተከላውን የምትመሩ አካላትም ችግኞቹን በወቅቱ በሚተከሉባቸው ሥፍራዎች በማድረስ፣ ሕዝቡን በማስተባበር ችግኞቹ ፈጥነው እንዲተከሉ ለማድረግ እስከ አሁን ከምታደርጉትም ጥረት በላይ ርብርብ ማድረግ ይኖርባችኋል።

በችግኝ ተከላው ስኬታማ መሆን የተቻለው ከእቅድ በላይ ችግኞችን በመትከል ፣ ሕዝቡንም ለእዚህ ታላቅ ሀገራዊ አጀንዳ ማሰለፍ በመቻልና በመሳሰሉት ብቻ አይደለም። ችግኝ ተከላው በአካባቢ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት እንዲችል በማድረግም ነው። ይህ ደግሞ የችግኝ እንክብካቤን የግድ ይላል። በዚህም በኩል ውጤታማ መሆን እየተቻለ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የችግኞች የጽድቀት መጠን እየጨመረ መምጣቱም ይህንኑ ይጠቁማል።

የችግኝ ተከላው ትሩፋቶች ገና ከወዲሁ መታየትም ጀምረዋል። መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ የሀገሪቱ የደን ሽፋን የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ከተጀመረበት የፈረንጆቹ 2019 ከነበረበት 17 ነጥብ ሁለት በመቶ ወደ 23 ነጥብ ስድስት በመቶ ከፍ ብሏል። ይህ ሌላው የመርሃ ግብሩ ስኬት ትልቁ ማሳያ ነው። በመርሀ ግብሩ ከተተከሉ ችግኞች መካከል እንደ አቮካዶ ያሉ የፍራፍሬ ተክሎች ችግኞች ይገኙበታል። እነዚህ ችግኞች ለፍሬ ደርሰው ለውጭ ገበያ ለመቅረብ የበቁበት ሁኔታም ይታያል። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው መርሀ ግብሩ ለአካባቢ አየር ንብረት መጠበቅ፣ ለምግብ ዋስትና መጠበቅ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ወዘተ. አስተዋጽኦ በማበርከት ግቡን ወደ መምታት እያመራ መሆኑን ነው።

እነዚህ ሁሉ ስኬቶች የዘንድሮውን የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ በስኬት ለማጠናቀቅ ትልቅ አቅም ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል። የዘንድሮው የዝናብ ይዞታ ለችግኝ ተከላ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይታመናል። ስለሆነም ይህን ምቹ ሁኔታም አሟጦ መጠቀምም ይገባል።

የክረምቱ ወቅት ገና እንደመያዙና በቀጣይም ችግኝ ለመትከል ሰፊ ጊዜ እንደመኖሩ በእቅድ የተቀመጡትን ችግኞች በሙሉ መትከል ይቻላል። ይህ ብቻም አይደለም፤ ይተከላሉ ተብለው ከሚጠበቁት ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችም በላይ ችግኞች መዘጋጀታቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ። ቀሪው ጊዜ እነዚህንም ችግኞች ለመትከል የሚያስችል እንደሚሆን ይታመናል። አሁን ያለነው ሀምሌ ወር አጋማሽ ላይ ነው፤ የክረምቱ ዝናብ እስከ መስከረም ድረስ ይዘለቃል ተብሎ ይታሰባል፤ በእነዚህ ጊዜያትም ችግኞችን መትከል ይቻላል፤ ጊዜ አለ በሚል መዘናጋት ውስጥ ባለመግባት ችግኞቹን አስቀድሞ መትከል ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን በእቅዱ ለመትከል ከተያዙት ችግኞችም በላይ ለመትከል፣ በችግኞች የመጽደቅ ምጣኔ ላይም የበለጠ ለውጥ ማምጣት፣ አጠቃላይ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብሩን ስኬት ወደ ላቀ የአፈጻጸም ምዕራፍ ማድረስም ይቻላል!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በዲፕሎማሲው መስክ ውጤታማ የሆነው 2016 በጀት ዓመት

እስማኤል አረቦ

ኢትዮጵያ ጥንታዊ ከሚባሉና ዘመን የተሻገረ የዲፕሎማሲ ታሪክ ካላቸው ጥቂት ሀገራት አንዷናት። ኢትዮጵያ በታሪክ ሂደት ባሳለፈቻቸው የ3ሺህ ዘመናት ታሪኳ ውስጥ በየዘመናቱ የዲፕላሚሲ ግንኙት በመፍጠርና ዐሻራ በማስቀመጥ ዛሬ ላይ የደረሰች ጥንታዊት ሀገር ነች። ኢትዮጵያ ጥንታዊ የዲፕሎማሲ ታሪካ ያላትና በየዘመናቱም የሀገሪቱን ጥቅም በዲፕሎማሲው መስክ ለማስከበር በርካታ ተጋድሎ ያደረጉ መሪዎችን ያፈራች ሀገር ነች።

ይኸው አኩሪ የዲፕሎማሲ ታሪክ ቀጥሎ በ2016 በጀት ዓመትም አመርቂ ውጤቶች ተገኝተዋል። በተለይም ዜጋ ተኮር የዲፕሎማሲ አካሄድና ጎረቤት ሀገራትን ማዕከል ያደረገው ስትራቴጂ ለኢትዮጵያ በርካታ ትሩፋቶችን እያስገኘላት ነው። በ2016 በጀት ዓመት ከጎረቤትና ከሌሎች ሀገራት ጋር ያለውን ግንኙነት በማሻሻል፣ በማጠናከርና ብሔራዊ ጥቅምን በማስከበር በኩል በርካታ ዲፕሎማሲ ሥራዎች ተከናውነዋል።

ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገር ጋር ያላትን በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ትብብር ተጠናክሮ እንዲቀጥል ለማድረግ በከፍተኛ አመራሮችና በሚኒስትሮች እንዲሁም በሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣናት ደረጃ የመረጃ ልውውጦችና የጋራ ኮሚሽን ስብሰባዎችን አከናውናለች። 12 የሚደርሱ የሁለትዮሽ ስምምነቶች ከጎረቤት ሀገራት ጋር ተፈራርማለች። ስምምነቶቹ በቱሪዝም፣ በትምህርት፣ በአቅም ግንባታ፣ በትራንስፖርት እና በሌሎች ዘርፎች ነው።

በሌላም በኩል አንዱ የሀገሪቱ ዲፕሎማሲ ማጠንጠኛ የሆነውን ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲን ከመተግበር አንጻር ፍርድ የተሰጣቸውና በእስር የሚገኙ ዜጎችን መቀያየር በሚቻልባቸውና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ከሀገራት ጋር መፈራረም ተችሏል። በዚህም በተለያዩ ሀገራት በስቃይና በእንግልት ውስጥ የቆዩ ዜጎች እፎይታ የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ሌላው የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ድል ተደርጎ የሚወሰደው ደቡብ ሱዳን የናይል ተፋሰስ የትብብር ማእቀፍ ስምምነትን ማጽደቋ ነው። አዲሷ የተፋሰሱ ሀገር የወሰደችውን ርምጃ “ታሪካዊ” ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አድንቀዋል። ስምምነቱ በደቡብ ሱዳን መጽደቁን፣ “ዲፕሎማሲያዊ እመርታ” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በበኩላቸው፣ ይህም “በናይል ተፋሰስ ቀጣናዊ ትብብር ለማድረግ ባለን የጋራ ምኞት ጉልህ ርምጃ ነው፤” ብለዋል።

በሌላ መጠሪያው “የኢንቴቤ ስምምነት” እየተባለ የሚታወቀው የናይል ተፋሰስ የትብብር ማእቀፍ ስምምነት፣ በደቡብ ሱዳን መጽደቁ፣ ስምምነቱ በተፋሰሱ ሀገራት ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን በቂ ድጋፍ የሚያስገኝ ነው።

ደቡብ ሱዳን ስድስተኛ ሀገር ሆና የትብብር ማእቀፍ ስምምነቱን መፈረሟ፣ ስምምነቱ “ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝና ወደ ተግባር እንዲሸጋገር የሚያስችል ነው። ይህም ለዘመናት በጉዳዩ ላይ ስትደክም ለቆየችው ኢትዮጵያ ትልቅ ድል ነው።

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማእቀፍ ስምምነትን አሥራ አንዱም የተፋሰሱ ሀገራት የሚጋሩትን የናይል ወንዝ፣ “ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ለግብጽ እና ለሱዳን ብቻ ያከፋፍላሉ፤” በሚል የሚተቹትን የቅኝ ግዛት ስምምነቶች በመሻር በአዲስ ለመተካት የሚያስችል ነው።

ስምምነቱ ለ11 ዓመታት ከዘለቀ ውይይት በኋላ፣ በ2002 ዓ.ም. (በአውሮፓውያኑ 2010) ግንቦት ወር ላይ በኢትዮጵያ፣ ታንዛኒያ፣ ዑጋንዳ፣ ሩዋንዳ እና ኬንያ ሲፈረም፣ ብሩንዲ በቀጣዩ ዓመት ስድስተኛ ሀገር ሆና ፈርማለች። ከእነዚህ ሀገራት መካከል ከኬንያ በቀር አምስቱ ስምምነቱን በየሀገሮቻቸው ሲያጸድቁ፣ ደቡብ ሱዳን ስድስተኛዋ የስምምነቱ አጽዳቂ ሀገር ሆናለች።

ይህንኑ አስመልክቶ የአሜሪካ ድምጽ (ቪኦኤ) እንደዘገበው የናይል ተፋሰስ የውሃ ምንጭ የሆኑት የላይኛው የተፋሰሱ ሀገራት፣ የትብብር ማእቀፍ ስምምነቱ፥ “ፍትሐዊ እና ምክንያታዊ አጠቃቀም” የሚለውን መርሕ የሚያሟላ መሆን እንዳለበት እንደሚገልጹና ስምምነቱ፥ “የውሃ ደህንነታችንንና ታሪካዊ ድርሻችንን ማረጋገጥ አለበት፤” የሚል አቋም ያላቸው ግብጽ እና ሱዳን በበኩላቸው፣ እስከ አሁን ስምምነቱን አለመፈረማቸውን ዘግቧል።

የደቡብ ሱዳን ውሳኔ፣ ከ11ዱ የተፋሰሱ ሀገራት ውስጥ የስምምነቱን አጽዳቂዎች ቁጥር ወደ ስድስት በማድረስ ወደ ተፈጻሚነት እንደሚያሸጋግረው ተናግረዋል። ይህም፣ ግብጽ እና ሱዳን፣ በቅኝ ግዛት ስምምነቶች መሠረት አለን የሚሉትን ታሪካዊ የውሃ መብት ጥያቄ የሚያስቀር ነው።

በሌላም በኩል ኢትዮጵያ በ2016 በጀት ዓመት ካገኘቻቸው ድሎች አንዱ ብሪክስን የሚመለከት ነው። ኢትዮጵያ የብሪክስ ቡድንን ለመቀላቀል ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነትን ማግኘቱን ተከትሎ በአሁኑ ወቅት ከመሥራቾቹ ቀጥሎ በሁለተኛ ረድፍ ላይ የቡድኑ ባለድርሻ ሆናለች። ይህም ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ዲፕሎማሲና የምጣኔ ሀብታዊ ድል ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ኢትዮጵያ የዚህ ብሎክ አባል መሆኗ በርካታ ጠቀሜታዎችን የሚያስገኙላት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ቀዳሚው የኢኮኖሚ ትብብር ነው። በዚህ የኢኮኖሚ ትብብር ኢንቨስትመንትን እና ንግድን ከማበረታት ጋር ተያይዞ በተለይ በአባል ሀገራት ዙሪያ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ሪሶርስ እና ገበያ አለ ተብሎ ስለሚታሰብ ብሪክስ አባል ሀገራት እርስ በእርሳቸው በሚያደርጉት የንግድ ልውውጥ እና የኢንቨስትመንት ሥራ ኢትዮጵያ ትልቅ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ትሆናለች ተብሎ ይታሰባል።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ፈጣን እድገት እያስመዘገቡ ከሚገኙ ሀገራት በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ እንደመሆኗ መጠን የብሪክስ አባል ሀገር መሆኗ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን ከዳር ለማድረስ ድጋፍ ይሆናታል። በተለይም ኢትዮጵያ እየገነባቻቸው ለሚገኙ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ብድርና እና ርዳታ ከማግኘት አንጻር ፋይዳው የጎላ ነው። የብሪክስ ማህበር የፈጠረው ኒው ዴቨሎፕመንት ባንክ (New Development Bank) በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ውስጥ ለመሠረተ ልማት እና ለዘላቂ ልማት ፕሮጀክቶች ሀብት የማሰባሰብ ዓላማ ያለው ከመሆኑ አንጻር ኢትዮጵያም የዚሁ ዕድል ተጠቃሚ የምትሆንበት ዕድል የሰፋ ነው።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ የኃይል ማመንጫ ግዙፍ ፕሮጀክቶችን፤ ሰፋፊ የግብርና ሥራዎችን፤ የመንገድ መሠረተ ልማቶችንና ኢንዱስትሪዎችን የምትገነባ ሀገር በመሆኗ ሰፊ መዋዕለ ንዋይ ያስፈልጋታል። ለዚህ ግብዓት የሚሆን ድጋፍ እና ብድር ከእነዚህ ሀገራት ይገኛል ተብሎ ይታሰባል። እንደ ቻይና እና ሩስያ ከመሳሰሉ ሀገራትም የብድር ተቀናሽና ስረዛ ለማግኘትም ዕድል ይሰጣል።

ከምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳው ጎን ለጎንም ኢትዮጵያን ዲፕሎማሲዊ ተሰሚነቷን የሚጨምረው ነው። በተለይም ኢትዮጵያ የምትከተለውን ከሁሉም ወገን ጋር አብሮ የመሥራት አካሄድ ለመተግበርና ከምዕራቡም ከምስራቁም ዓለም ጋር በወዳጅነት ለመዝለቅ የምትከተለውን ሚዛን የጠበቀ ግንኙነት ወደ መሬት ለማውረድ የሚያስችላት ነው።

ለኢትዮጵያም ሆነ ለአባል ሀገራቱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የብሪክስ ስብስብ በ2016 በሩሲያ ሞስኮ ስበሰባውን አካሂዷል። ኢትዮጵያም በዚህ ከፍተኛ ጉባዔ ላይ የተሳተፈች ሲሆን ስብሰባውም ኢትዮጵያ ከብሪክስ አባል ሀገራት ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ኢኮኖሚ ትብብሯን ለማጠናከር የረዳት ነበር።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ እያስመዘገበችው ያለው ውጤት የሀገሪቱን ተሰሚነት ያሳደገና በርካታ ጥቅሞችንም ይዞ የመጣ ነው። በአራቱም አቅጣጫ ያለምንም አድሎና ወገናዊነት እያሳካችው ያለው የዲፕሎማሲ ድል ሀገሪቱ በርካታ ወዳጆችን እንድታፈራና በሪዮታለም የታጠረውን የዓለም አካሄድ ተሻግራ ጥቅሟን እንድታረጋግጥ አድርጓታል።

## ነፃ ሃሳብ

# ‹‹ክፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል››

**ኃይሉ ሣሕለድንግል**

ባለፉት የለውጥ ዓመታት መንግሥት፣ አርሶ አደሮች፣ ባለሀብቶችና ሌሎች የልማት ኃይሎች ባካሄዷቸው ዘርፈ ብዙ የልማት ሥራዎች በግብርናው፣ በኢንዱስትሪው፣ በቱሪዝሙ፣ በኃይል ልማትና በሌሎች ዘርፎች ተጠቃሽ ውጤቶች ታይተዋል። በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት፣ በተኪ ምርቶች፣ በቱሪዝም መዳረሻ ልማት፣ በዓባይ ግድብ ግንባታ የተከናወኑ ተግባሮችና የተገኙ ውጤቶች ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳሉ።

እነዚህ ስኬቶች የተመዘገቡት ደግሞ ልማቶቹ እንዲስተጓጎሉ የሚያደርጉ የውስጥና የውጭ ጫናዎች በከፍተኛ ደረጃ ፈተና ሆነውም ነው፤ አንዳንዶቹ ጫናዎች በኢትዮጵያ ላይ ብቻ የደረሱ አይደሉም፤ በሌሎች ሀገሮች ላይም ጫና ያሳደሩት እንደ ኮቪድ 19 ያሉት ፈተናዎች እንደ ኢትዮጵያ ባሉት በኢኮኖሚ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ በሚገኙ ሀገሮች ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል።

ወረርሽኙን ተከትሎ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ሥራ ላይ በዋለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅም ሆነ በሌሎች የበሽታው ስርጭት ባስከተላቸው ጫናዎች ሳቢያ ዜጎች ከሥራ ውጪ የሆኑበት፣ ተቋማት ሥራ ያቆሙበት ሁኔታ ወዘተ ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

የሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት ሌላው ሀገሪቱን ለብዙ ቀውስ (ለማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ) የዳረጋት ትልቅ ችግር መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና መንግሥት ‹‹ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር ብሎ አልነበረም›› ጦርነቱን ያካሄድ የነበረው። ጦርነቱን በድል ለመወጣት ይደረግ ከነበረው እንቅስቃሴ ጎን ለጎን ለልማቱ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሠራ በማድረግም ጭምር እንደነበር ይታወሳል። በዚህም በኢኮኖሚውም ውጤታማ ለመሆን ብዙ ጥረት ተደርጓል።

ሀገሪቱ ለኢኮኖሚዋም ይህን ያህል ጥንቃቄ አርጋ ብትሠራም፣ ከዚያ ወሳኝ የጦርነት ወቅት እንዲሁም ከዓባይ ግድብ ግንባታ ጋር ተይይዞ የተደረጉባት ጫናዎች በኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድረዋል። ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን ለማስጠበቅ እንዲሁም የዓባይ ግድብ ግንባታዋን ለመቀጠል የምታደርጋቸውን ጥረቶች ለማሰናከል የተደረጉት ጫናዎች ለሀገሪቱ ልማት ከባድ ፈተናዎች ነበሩ።

የመንግሥትን እጅ በመጠምዘዝ በጫና ለማንበርከክ የተደረገው ጥረት ብዙ ርቀት የተጓዘም ነበር። እንደ አሜሪካ ያሉት ሀገሮች አምባሳደሮቻቸውን ከኢትዮጵያ እስከ ማስወጣት ደርሰዋል፤ ከሰሐራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገሮች ከቀረጥ ነፃ ምርቶቻቸውን ለአሜሪካ ገበያ ከሚያቀርቡበት /አጎአ/ ዕድል ኢትዮጵያ ተጠቃሚ እንዳትሆን ተደርጓል። ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ብድርና እርዳታ መስጠት ካቆሙ የቆዩ ቢሆንም፣ ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ /እስከ አሁንም ድረስ/ በዚሁ አቋማቸው ጸንተዋል።

ጦርነቱ ያወደማቸው፣ ከሥራ ያስተጓጎላቸው ኢንዱስትሪዎች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም፤ በግብርናው መስክም ቢሆን በማዳበሪያ ግዥ የተፈጠረው ጫናም በቀላሉ የሚታይ አይደለም። የውጭ ምንዛሪው እያለም ማዳበሪያ መግዛት ፈታኝ እንደነበር ይታወሳል። ከኢትዮጵያ አትግዙ፤ ለኢትዮጵያ አትሽጡ የሚሉም ጫናዎች ብዙ ነበር።

ልማት በራስ አቅም ሊካሄድ ቢችልም ልማቱን ለማሳለጥ በሚደረገው ጥረት ወሳኝ የሆነው የውጭ ምንዛሪ ሊገኝባቸው የሚችልባቸው እንደ ብድርና ርዳታ ያሉት የፋይናንስ አማራጮች ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በተለይ ብድርን እንኳን ኢትዮጵያ ያደጉት ሀገሮች ጭምር በእጅጉ ይፈልጉታል፤ ብድር ለኢትዮጵያ የልማት ግብዓት ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር የለውም።

ይህ ብድርና ርዳታ የሚገኝባቸው አጋር ሀገሮችና ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት ብድርና እርዳታ ላለመስጠት መወሰናቸው ልማቱን በሆነ መልኩም ቢሆን አያንገራግጨውም ተብሎ አይታሰብም፤ አልተንገራገጨም ማለትም አይቻልም። የልማት አጋሮችን፣ ሠላምን፣ የውጭ ገበያ ማጣት፣ ወዘተ በልማት ላይ ችግር እንደሚፈጥር ይታወቃል።

እርምጃዎቹን መሠረት በማድረግ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ እቃ እንዳያገኙ፣ የኢትዮጵያ ምርቶች ወደ ለመዱት መዳረሻቸው እንዳይሄዱ በማዕቀብ ጣዮች ወይም ጫና ፈጣሪዎች በኩል ብዙ ጥረት ተደርጓል። ይህቺ ሀገር የኢንዱስትሪ ግብዓት ብቻ ሳይሆን፤ ለሰው ልጅ በእጅጉ የሚያስፈልጉ ሰብዓዊ እርዳታዎችን ጭምር እንዳታገኝም ተደርጋም እንደነበር የሚታወስ ሀቅ ነው።

**ለልማት አንድ አቅም ተደርጎ የሚታሰበው የውጭ ብድርና ርዳታ በተለያዩ ጫናዎች ምክንያት ከኢትዮጵያ እንዲፋታ ቢደረግም፣ መንግሥት የሀገር ውስጥ አቅምን አሟጦ በመጠቀም ለውጥ አምጥቷል**

በሀገሪቱ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ከተሰማሩ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ሀገራቸው የሄዱበት፣ ሌሎች ወደ ሀገሪቱ እንዳይመጡ የሆነበት ሁኔታም ነበር። በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅትም እንዲሁ በርካታ ኢንዱስትሪዎች ሥራ ያቆሙበት ሁኔታ መታየቱ ይታወቃል።

በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የተከሰቱ ግጭቶች ያጠፉት የሰው ሕይወት፣ ያጎደሉት አካል፣ የፈጠሩት የእንቅስቃሴ ገደብ፣ ያወደሙት ሀብት፣ ለድንጉጡ ኢንቨስትመንት /በተለይ ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት/ ከፍተኛ ፈተናዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ማንም አይስተውም። በጦርነቱ ከወደሙ፣ ከተዘረፉ ኢንዱስትሪዎች፣ ሥራቸው ከተስተጓጎለ ኢንዱስትሪዎች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንቱም ሆነ ሌሎች ኢንቨስተሮች ምን እርምጃ ሊወስዱ እንደሚችሉ መገመት አይከብድም።

በዚህ ሁሉ ፈተና ውስጥ የቆየች ሀገር ልማቷን ለማስቀጠል የምትጠይቀውን ብድርና ርዳታ የሚከለክሉ የፋይናንስ ተቋማትና እነሱን የሚዘውሩ ያደጉ ሀገሮች ብድርና ርዳታ ማስከልከላቸው አንሶ ሀገሪቱ ቀደም ሲል የተበደረችውን ከፍተኛ መጠን ያለው ብድር በዚያ ክፉ ቀን እንድትከፍል ጫና ተደርጎባታል። ጫና ብቻም ሳይሆን እንድትከፍል ተደርጋለች።

የውጭ ኃይሎች ይህን ሁሉ ያደረጉት የኢትዮጵያ መንግሥት ጫና ሲበዛበት በቀደድንለት ቦይ ይፈሳል ብለው በማሰብ ነው። መንግሥትን በጫና ብዛት በማንበርከክ የፈለጉትን ሊፈጽሙ አስበው ነበር። ይህ ግን ሊሆን አይችልም ! ነበርና አልሆነም።

ሀገሪቱና ልጆቿ ፈተና አጠንክሯቸው እንጂ አላንበረከካቸውም፡፤ መለኛ አርጓቸው፤ ነገሮችም ጫና ፈጣሪዎች እንዳሰቡትና እንዳቀዱት ሳይሆኑ ሀገሪቱና ልጆቿ እንዳሰቡትና እንዳቀዱት ቀጠሉ። ሀገሪቱም በብዙ ፈተና ሥርታ ካገኘችው ሀብት ትርጉም ያለው የብድር መጠን ስትከፍል ቆይታለች፤ እየከፈለችም ትገኛለች።

የለውጡ መንግሥት ባጋጠሙት ብዙ ፈተናዎች ሳይፈታና ሳይረታ፣ ይልቁኑም ችግርን እንደ መውጫ በማድረግ ያሉትን የሀገር ውስጥ ሀብቶች አሟጦ በመጠቀም ጫና ፈጣሪዎቹ እንዳሰቡት ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ እንዳሰቡት፣ እንደተገበሩትም ሆኖ በፈተና ውስጥ አያሌ ስኬቶችን ማስመዝገብ ተችሏል።

በሀገራችን አንድ አባባል አለ፤ ‹‹ክፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል›› የሚል። ምንም እንኳን መንግሥትን ለማንበርከክ በሚል በሀገሪቱ ላይ በርካታ ጫናዎችን ያሳደሩት ሀገሮች /በጥሬው ትርጉሙ/ ለእኛ ጎረቤት ሀገሮች ባይሆኑም፣ ቅርበታቸው፣ ተፅዕኖ ፈጣሪነታቸው፣ ቀደም ሲል ከሀገሪቱ ጋር የነበራቸው እጅ ለእጅ ተያይዞ መጓዝ ሲታሰብ የጎረቤት ያህል ሊቆጠሩ የሚችሉ ሀገሮች ናቸው ሊባሉ ይችላሉ። እነዚህ ሀገሮች/በአብዛኛው ምዕራባውያን ናቸው፤ ለነገሩ በዚያ ክፉ ቀን ዜጎቻቸውን ያስወጡ የአፍሪካ ሀገሮችም ነበሩ/ የጎረቤት ያህል ለኢትዮጵያ ቅርብ ናቸው።

ቴክኖሎጂ ዓለምን አንድ መንደር ባደረገበት ዘመን ጎረቤት የማይሆን ሀገር የለም። እናም እነዚያ ሀገሮች በድንበር ባይዋሰኗትም ጎረቤት ሀገሮች ናቸው።

ከለውጡ በፊት አንድ ወቅት ላይ ኩዌቶች ላንጋኖ አካባቢ አንድ የቱሪስት ከተማ /12 ሺ ሕዝብ ሊያኖር የሚችል/ ሊገነቡ የመሠረት ድንጋይ ተቀምጦ ነበር፤ በሥነሥርዓቱ ላይም የወቅቱን የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ፕሬዚዳንትን ጨምሮ በርካታ ከፍተኛ ባለሥልጣናትም ተገኝተዋል። /ዜናውን በወቅቱ በብሔራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ ነው የተከታተልኩት/ ንግግር ካደረጉት መካከል አንድ የኩዌቱ ሰው ኢትዮጵያና ኩዌት ጎረቤት ሀገሮች ናቸው ሲሉ መናገራቸውን አስታውሳለሁ፤ እኔም እንዴት ሆኖ እያልኩ ሳሰላስል ለእዚህ አባባላቸው ማብራሪያ ሲሰጡ ከአዲስ አበባ ኩዌት ያለውን የአራት ሰዓት የበራራ ርቀት የጉርብትና ያህል ወስደው ነው። ትክክል ነው፤ ያስኬዳል። እኔም ያኔ ያንን ሁሉ ጫና ያሳደሩብን ሀገሮችን እንደ ጎረቤት መውሰዴ አንድም ለእዚህ ነው።

እናም ክፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል እንደተባለው፤ እነዚህ ሀገሮችና አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማት በሀገሪቱ ላይ የፈጠሩት ጫና ሀገሪቱ ችግርን እንደ ልማት መሣሪያ፣ የዜጎችን አቅም እንደ ዋነኛ የልማት መሣሪያ አድርጋ እንድትጠቀም አድርጓል። ያንን ሁሉ ተጠቅማም ነው ባለፉት ዓመታት ተጠቃሽ የልማት ስኬቶችን ማጣጣም ውስጥ የገባችው። ኢትዮጵያ የአጎዋ ዕድልን ተጠቃሚ እንዳትሆን መከልከሏን ተከትሎ የኢንዱስትሪ ውጤት የሆኑ ምርቶችን ሊቀበሉ የሚችሉ ሌሎች ሀገሮችን ማማተር ውስጥ ተገብቷል፤ ቻይና የኢትዮጵያን የኢንዱስትሪ ውጤቶች ለመቀበል ፍላጎት ያሳየችውም ይህንኑ ተከትሎ ነበር፤፤

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በቅርቡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ሀገሪቱ በተጠናቀቀው 2016 በጀት ዓመት በብዙ ፈተና ውስጥ ሆናም አያሌ ለውጦችን ማስመዝገብ መቻሏን ማስታወቃቸው ይታወሳል። እነዚህ ስኬቶች ኢትዮጵያውያን ችግርን እንደ መውጫ ተጠቅመው፣ የዜጎችን አቅም አሟጦ ለመጠቀም በተከናወኑ ተግባሮች የተመዘገቡ ናቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በወቅቱ እንዳሉት፤ ዕዳ ያጎበጠው ኢኮኖሚ ያላት ሀገር ከለውጡ ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት ኮሜርሻል ብድር አልወሰደችም፤ አንድ ዶላር ኮሜርሻል ብድር ላለፉት ስድስት ዓመታት አልወሰደችም። በአንጻሩ ግን የአበዳሪ ተቋማት ዕዳ ወደ ልጆቿ መሸጋገር የለበትም በሚል ጽኑ እምነት ብድሯን ስትከፍል ቆይታለች፤ ዛሬ ኢትዮጵያ ያለባት የውጭ እዳ ወደ 17 ነጥብ አምስት በመቶ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርቷ /ከጂዲፒዋ/ ዝቅ ብሏል። ይሄ ትልቅ ድልና ትልቅ ዜና ነው ሲሉ መግለጻቸው ይታወቃል።

ከሰሐራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገሮች በአማካይ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርታቸው /ጂዲፒ/ ስልሳ በመቶ ዕዳ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከዛም በላይ ዕዳ ያለባቸው ሀገራት እንዳሉም አስታውቀዋል። ዕዳን ወደ 17 በመቶ ማውረድ መቻል እጅግ በጣም ተስፋ ሰጪ መሆኑንም አመልክተው፣ በሚቀጥሉት ዓመታት በሚደረጉ ርብርቦች ደግሞ ዕዳው ከ10 በመቶ በታች መውረድ እንዳለበትም አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ሀገሪቱ ባለፉት ዓመታት ከ10 ቢሊዮን ዶላር በላይ ዕዳ ከፍላለች፤ የከፈለችው ዕዳ ደግሞ በቀደመው መንግሥት ወቅት የተወሰደ ብድር ነው፤ ‹‹ወደ ልጆቻችን ዕዳ እንዳይሻገር አንድ እርምጃ ወደፊት መጓዝ ችለናል። ተጨማሪ እርምጃዎች መውሰድ ግን ይጠበቅብናል" ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ከተከማቸ ብድር ውስጥ ትርጉም ያለውን ያህል ዕዳ መክፈል መቻል አንድ ትልቅ ስኬት ነው፤ ምንም ሳይበደሩ ይህን ያህል ከፍተኛ መጠን ያለው ብድር መክፈል መቻል ደግሞ በራሱ ሌላ ትልቅ ስኬት ነው። የለውጡ መንግሥትም ያደረገው ይህንኑ ነው።

ጫና ሊያሳድሩብን የፈለጉና በብዙ መልኩም ጫና ያደረጉብን ሀገሮችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ሳያውቁት ጠንካራ ሀገር ሆነን እንድንወጣ አድርገውናል፤ በተኪ ምርት ላይ በተከናወነው ተግባር የተገኘው ውጤትም ሌላ ጫና የወለደው ስኬት ነው።

እንደሚታወቀው የሀገራችን የወጪና ገቢ ንግድ ሚዛን ሲታይ ቀደም ሲልም አንስቶ ከፍተኛ ክፍተት ይስተዋልበታል፤ የገቢ ንግዱ ሚዛን ከወጪ ንግዱ በእጅጉ ይሰፋል። ብዙ ቢሊዮን ዶላሮችን የሚጠይቁ ምርቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ስናስገባ፣ ወደ ውጪ ከምንልካቸው ምርቶች የምናገኘው የውጪ ምንዛሪ ግን ከዚህ በእጅጉ ያነሰ ነው።

ሀገራችን በርካታ ምርቶችን ለውጪ ገበያ ብታቀርብም የግብርና ምርቶችን ለውጪ ገበያ በማቅረብ ግን በእጅጉ ትታወቃለች። የግብርና ምርቶቹም ብዙ ዓይነት ናቸው። ቡና፣ የቅባት እህሎች፣ ጥራጥሬ፣ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ የቁም እንስሳት፣ ሥጋና የሥጋ ውጤቶች፣ ጫት፣ ወዘተ በስፋት ትልካለች። እንደ ወርቅ፣ ኦፓል ያሉ ማዕድናትን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ አንዳንድ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ደግሞ ለጎረቤት ሀገሮች ትልካለች። በዚህ ሁሉ የውጭ ምንዛሪ ታገኛለች።

ለውጭ ገበያ የምትልካቸውን ምርቶች መጠንና ጥራት ለማሳደግ፣ የምርቶቹ መዳረሻ ሀገሮችን ለማስፋት፣ የምርቶቹን አይነትም ለማብዛት እንዲሁም ጥራታቸውን ለማስጠበቅም እንዲሁ በትኩረት ሠርታለች።

ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቁ የገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለማምረትም ብዙ ርቀት ተጉዛ ውጤቶችን ማየት ጀምራለች። ለከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልገውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ማምረት ጀምራለች ብቻ ሳይሆን ከውጭ የሚመጣውን የድንጋይ ከሰል ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እየሠራች ናት። የቢራ ገብስ ከውጪ ማስመጣት ትታለች። ስንዴ በሀገር በስፋት በማምረትም ስንዴ ከውጪ ከመግዛት ወጥታለች። በነዳጅ ጥገኛ ሆኖ የኖረው የትራንስፖርት ዘርፏ የኤሌክትሪክ ኃይል ወደ መጠቀምም ገብቷል። ይህም ነዳጅ ከውጪ ለማምጣት የሚወጣውን የውጪ ምንዛሪ ለመቀነስ የበኩሉን ሚና ይወጣል።

በአጠቃላይ ግብርናን ጨምሮ በኢንዱስትሪና በሌሎች ዘርፎች አንዳንድ ምርቶች በተደረገ የገቢ ምርት መተካት /ኢምፖርት ሰብስቲትውሽን/ ሥራ ባለፈው በጀት ዓመት ብቻ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚያወጡ የገቢ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ማምረት ተችሏል።

በተኪ ምርቶች ላይ የተከናወነውን አስመልክተው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲያብራሩ ስንዴ አንዱ ተኪ ምርት መሆኑን ጠቅሰው፣ ‹‹በስንዴ ላይ በተከናወነው ተግባር ብዙ ብር አስቀርተናል›› ብለዋል። ‹‹የፋብሪካ ምርቶች 40 በመቶ ደርሰናል። የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ምርቶችን መጠቀም ጀምረናል። ይሄ እጅግ በጣም ተስፋ ሰጪ ነገር ነው።›› ሲሉም ተደምጠዋል።

በተኪ ምርት ላይ እየተከናወነ ያለው ተግባር በንግድ ሚዛኑ ያለውን ክፍተት ለማጠበብ አስተዋፅዖ እንዳለው በእጅጉ ይታመናል። በተኪ ምርት ላይ የታየው አፈጻጸም ወደ 50፣ 60፣ 70 እያደገ ከሄደ፣ ገቢ ምርትን ከተካን፣ የወጪ ምርትን /ኤክስፖርት/ ካሳደግን በገቢና ወጪ ንግድ መካከል ያለው የንግድ ክፍተት /ትሬድ ዴፊሴት/ እየቀነሰ ከሄደ ጤናማ የሆነ ኢኮኖሚ ለመገንባት በእጅጉ ያግዛል ሲሉ ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስታወቁት ።

የሰሜኑ ኢትዮጵያ ጦርነት በፕሪቶሪያው ስምምነት መሠረት ሲቆም ዓለም አቀፍ ተቋማትና ግብረ ሠናይ ድርጅቶች የርዳታ አቅርቦት ማቆማቸው ይታወሳል፤ ይህን ክፍተት ለመሙላት መንግሥት በሀገር ውስጥ አቅም የርዳታ አቅርቦት ለመሙላት ርብርብ አድርጎ የተሳካ ሥራ የሠራበት ሁኔታም ሌላው የውጪ ኃይሎች ጫና የወለዳቸው መፍትሔዎቻችንና ስኬቶቻችን ናቸው።

ለዚህ ሁሉ ስኬት ለመድረስ በየዘርፉ ብዙ ተሠርቷል፤ ለልማት አንድ አቅም ተደርጎ የሚታበው የውጭ ብድርና እርዳታ በተለያዩ ጫናዎች ምክንያት ከኢትዮጵያ እንዲፋታ ቢደረግም፣ መንግሥት የሀገር ውስጥ አቅምን አሟጦ በመጠቀም ለውጥ አምጥቷል። ጫና ሊያሳድሩብን የሞከሩ ኃይሎች ቢበረቱብንም፣ የልማት አቅማችንን አይተን በራሳችን አቅም እንድንሠራ አማራጭ መንገድ እንድንፈልግ አበርትተውናል። ለእዚህም ነው ‹‹ክፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል›› ያልነው።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ሀገር በቀል እውቀትን ከዘመናዊው ያጣመረው የእንስሳት መድኃኒት ምርምር

ማሒሌት አብዱል



ቢክሲሳ ኡርጌን (ዶ/ር)

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሃብቷ በአፍሪካ ቀዳሚዋ በዓለም ደረጃ ከፊተኞቹ መካከል ብትጠቀስም፣ ከዘርፉ የሚገባትን ያህል ተጠቃሚ እንዳልሆነችም ይታወቃል። ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ችግሮች በምክንያት ይነሳሉ። የእንስሳት ሃብቱን ምርታማነት ለማሳደግ ከቁጥር ባሻገር ጤናማና ዘመናዊ የሆነ የእንስሳት እርባታ ሥርዓት ያለመዘርጋቱ በዋነኝነት ይገለጻል። ሥርዓቱ አሁንም ድረስ ኋላቀር በመሆኑ በእንስሳቱ ላይ የሚያጋጥሙ በሽታዎችን መከላከል የሚያስችል አቅም እንዳይጎለብት ሆኖ ቆይቷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሃገሪቱ ለእንስሳት ሕክምና እና መድኃኒት በየዓመቱ ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ታወጣለች። የዚህ እንስሳት መድኃኒት ዋጋም ውድና ተደራሽ ባለመሆኑ ምክንያት አሁንም ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው አርሶና አርብቶ አደር ባሕላዊ የእንስሳት መድኃኒቶችን እንደሚጠቀም መረጃዎች ያመለክታሉ። እነዚህ ባሕላዊ መድኃኒቶች ፈዋሽነታቸውና ፍቱንነታቸው ምንም እንኳ በሳይንሳዊ መንገድ ባይረጋገጥም አርሶ አደሮቹም ሆነ አርብቶ አደሮች ዛሬም ድረስ እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ባሕላዊ መድኃኒቶችን ለእንስሳት ሕክምና በመጠቀም ሕንድና ቻይና የተሻለ ተሞክሮ አላቸው። እነዚህ ሃገራት ከውጭ የሚያስገቡትን የእንስሳት መድኃኒት በሃገራቸው ምርት ከመተካት አልፈው ለሌሎች ሃገራት በመሸጥ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ማግኘት እየቻሉም ነው።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በርካታ መድኃኒታማ ዕፅዋቶች እንዲሁም ሃገር በቀል እውቀቶች ቢኖራትም፣ በዘመናዊ መንገድ በመፈተሽና እሴት በመጨመር ጥቅም ላይ ማዋል ባለመቻሏ ከውጭ በሚገቡት ምርቶች ላይ ጥገኛ እንድትሆን አድርጓታል።

ሃገሪቱ በየጊዜው ለእንስሳት መድኃኒት የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ መታደግ ያስችል ዘንድ በምርምር ዘርፍ ምን እየተሠራ ነው? ስንል በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርምር ዘርፍ አስተባባሪ የሆኑትን ቢክሲሳ ኡርጌን (ዶ/ር) ጠይቀናል። እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ ኢንስቲትዩቱ የሃገሪቱን የእንስሳት ሃብት ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ፤ ሃገራዊ የልማት ግቦችን መሠረት ያደረጉ ሰፋፊ የምርምር ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ለዚህም ይረዳው ዘንድ በዘርፉ በብሔራዊ ደረጃ የምርምር ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት፤ የምርት ጥራትን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ሥራዎችን በማዕከል፣ በአርሶ አደርና አርብቶ አደር ደረጃም እየተሠራ ነው።

በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ሃገር በቀል እውቀቶችን መሠረት በማድረግ መድኃኒታማ ዕፅዋቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ የምርምር ሥራዎች መሠራታቸውን አስተባባሪው ይጠቅሳሉ። በማዕከሉ የሚከናወነው ምርምርም ሆነ የሚገኘው ውጤት ሃገሪቱ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት እያደረገች ላለችው ሁለንተናዊ ጥረት አስተዋፅዖ ማበርከት በሚያስችል መልኩ ታስበው የተቀረፁ ስለመሆናቸውም ያስረዳሉ።

ሃገር በቀል እውቀቶችና ዕፅዋቶች ላይ ምርምር በማድረግና ሥራ ላይ በማዋል በርካታ የዓለም ሃገራት ተጠቃሚ መሆናቸውን ቢክሲሳ (ዶ/ር) ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ግን በተሻለ መልኩ ሃገር በቀል እውቀትም ሆነ የዕፅዋት ሃብት ቢኖራትም በዘመናዊና ሳይንሳዊ መንገድ ባለመቀመሯ የእንስሳት ሃብቷን ከበሽታ ለመታደግ ያለመቻሏን ቁጭት ሊፈጥር ይገባል ይላሉ። ይህንን ታሪክ ለመቀየር በተለይ ባለፉት አምስት ዓመታት እነዚህን ሃገር በቀል እውቀቶች በመጠቀም ሃገሪቱ እያወጣች ያለችውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት ኢንስቲትዩቱ በብሔራዊ ደረጃ ፕሮጀክት ቀርፆ ሰፊ ርብርብ እያደረገ መሆኑን ያመለክታሉ።

‹‹እነዚህን ሃገር በቀል እውቀቶችንና፤ በተፈጥሮ ያገኘናቸውን መድኃኒታማ ዕፅዋቶችን የልማት ሥራዎች በቤተ-ሙከራ እንዲታገዙ በማድረግና፤ በቴክኖሎጂ የተደገፉ አዳዲስ አሠራሮችን ማውጣት ችለናል›› ሲሉም ይገልጻሉ። በዋናነትም በተደጋጋሚ በሚከሰቱና አዲስ

**ባሕላዊውን ከዘመናዊ ምርምር በማጣመር የተገኙት መድኃኒቶች በዋናነት ከዚህ ቀደም እንደሀገር በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ የእንስሳት በሽታዎችን መከላከል የሚያስችሉ ናቸው**

ሊከሰቱ በሚችሉ የእንስሳት በሽታዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ የምርምር ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውንም ያብራራሉ። በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት በሽታችን በመለየት፣ ለመከላከልና ምላሽ በመስጠት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በማውጣትም የበኩሉን ድርሻ እየተወጣ ነው ሲሉ ይጠቅሳሉ።

አስተባባሪው እንዳስታወቁት፤ በጣም በስፋት ስንሠራበት የነበረው የኢትኖ ቨተርነሪ ምርምር ዘርፍ ነው፤ ይህም ባሕላዊ የእንስሳት መድኃኒቶች ላይ ያተኩራል፤ በተለይም በሁሉም ክልሎች በሚባል ደረጃ የሚገኙ በማኅበረሰቡ በፈዋሽነታቸው የሚታወቁ መድኃኒታማ እፅዋቶችን በመሰብሰብ፤ በማባዛት፣ በቤት ሙከራ ሳይንሳዊ ምርምር በማካሄድና እሴት በመጨመር ስድስት የተለያዩ መድኃኒቶችና ኬሚካሎችን ማውጣት ተችሏል።

ባሕላዊውን ከዘመናዊ ምርምር በማጣመር የተገኙት መድኃኒቶች በዋናነት ከዚህ ቀደም እንደሃገር በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ የእንስሳት በሽታዎችን መከላከል የሚያስችሉ መሆናቸውን አስተባባሪው ገልጸዋል። ለአብነትም እንደ ፈንግል ያሉ የዶሮ በሽታዎችን፣ በተደጋጋሚ የሚከሰቱ የወተት ላሞች በሽታዎችን ለማከም የሚያስችሉ መሆናቸውንም ይጠቅሳሉ። ‹‹በተለይ የእንስሳት የጡት፣ የቆዳ፣ የሳልና ጥጆችን የሚገድሉ በሽታዎችን የሚከላከሉ ናቸው›› ሲሉም ያስረዳሉ።

ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገቡት መድኃኒቶች በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ ባለመሆናቸው ምክንያት በተለያየ ጊዜ የእንስሳት መሞት በስፋት እንደሚያጋጥም የሚጠቅሱት ቢክሲሳ (ዶ/ር)፤ አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ እነዚህ ከውጭ የሚገቡት መድኃኒቶችን የማግኘት ዕድሉ ቢኖረውም እንኳን ተጓዳኝ የሆኑ ችግሮችን የሚያስከትሉ በመሆናቸው ተመራጭ አይደሉም ሲሉም ያስገነዝባሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ከውጭ የሚገቡ መድኃኒቶች የመድኃኒት መላመድ ችግሮችን የሚያስከትሉ ናቸው፤ በተጨማሪም በተለያዩ የእንስሳት ተዋፅዖ ውጤቶች ላይም የመድኃኒት ቅሪት እንዲኖርና በተጠቃሚዎች ጤና ላይ አሉታዊ ችግር ሊያመጡ ይችላሉ። እነዚህን ሁሉ ችግሮች በመፍታት ረገድ ከሃገር በቀል ዕፅዋቶች የተገኙት መድኃኒቶችና እና ቴክኖሎጂዎች ውጤቶች ከፍተኛ አስተዋፅዖ አላቸው።

አስተባባሪው እነዚህ በምርምር መድኃኒቶች ከውጭ ይገቡ የነበሩትን ከመተካት ባለፈ፤ የውጭ ምንዛሪ በመታደግ ያላቸውን አበርክቶ ተጠይቀው ሲመልሱ ‹‹በብሔራዊ ደረጃ ከተሠሩት የምርምር ሥራዎች መካከል ለምሳሌ ብንጠቅስ ‹አፕሮሊየም› የሚባል የዶሮ መድኃኒት ኢትዮጵያ ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ነው የምታስገባው፤ ሆኖም አሁን በተሠራው የምርምር ሥራ በሃገር በቀል ዕፅዋት መተካት ተችሏል። ይህም በመሆኑ ሃገሪቱ ለመድኃኒት ግዢ የምታወጣው ወጪ ይቀንሳል›› በማለት ይገልፃሉ። የእንስሳት ጡት በሽታን ለማከም ለሚያገለግለው አንድ መድኃኒት 30 ሺ ብር ወጪ እንደምታደርግ ጠቅሰው፤ ከአሉቬራ (ሬት) በሚሠራው መድኃኒት መጠቀም ቢቻል ግን ይህንን ወጪ ማስቀረት እንደሚቻል ነው የተናገሩት።

ኢንስቲትዩቱ ያወጣቸውን ቴክኖሎጂዎችና የምርምር ውጤቶች የማስፋፋት ሥራ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከመድኃኒት ፋብሪካዎች በተጨማሪ ለኬሚካል ኢንዱስትሪዎችም ዋነኛ ግብዓት በመሆናቸው በሃገር ደረጃ የማስፋፋት ሥራ ሊሠራ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። በተለይ በአሁኑ ወቅት መድኃኒቶቹን ከውጭ የሚያስመጡ ኢንዱስትሪዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡም ቢክሲሳ (ዶ/ር) ጠይቀዋል።

‹‹በአሁኑ ወቅት በርካታ የምርምር ሥራዎች እየሠራን ብንገኝም እነዚህን ቴክኖሎጂዎች አባዝቶ ለተጠቃሚዎች በአግባቡ ማድረስ ላይ ክፍተት አለ›› የሚሉት አስተባባሪው፤ በተለይም በአርብቶአደር አካባቢ የሚከሰቱ በሽታዎችን ለመከላከል የሁሉም ርብርብ ወሳኝ እንደሆነም አስገንዝበዋል። ‹‹ለምሳሌ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የገንዲ በሽታ በስፋት ያጋጥማል፤ ይህንን በሽታ በመከላከል ረገድ ሰፊ ምርምር እናደርጋለን። ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ብቻ ከአንድ ሺ በላይ የሚሆኑ አርብቶ አደሮች የተለያዩ የእንስሳት ጤና ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ ሆነዋል›› ይላሉ። ይሁንና ከዚህም በላቀ ቁጥር ተጠቃሚ ለማድረግ የሌሎች አካላት ድጋፍ ወሳኝ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

በሌላ በኩልም ከሁለት ዓመታት በፊት በበርካታ የሃገሪቱ አካባቢዎች ተደጋጋሚ የሆነ የዶሮ ወረርሽኝ በሽታ ይከሰት እንደነበር ቢክሲሳ (ዶ/ር) አንስተው፤ እሳቸው እንዳሉት፤ ኢንስቱትዩቱ በእነዚህ የዶሮ በሽታዎች መድኃኒቶች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሰፊ ሥራ ሠርቷል። በተለይ በክትባት ላይ የማሻሻያ ሥራ በመሥራት አበረታች ውጤት ማግኘትም ተችሏል። በተጨማሪም ለኅብረተሰቡ ስለ ዶሮ በሽታና የክትባት አጠቃቀም በቂ እውቀት እንዲኖረው ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ተከናውኗል። ይህም በመሆኑ በሌማት ትሩፋቱም ሆነ በሌሎች የልማት መርሐ ግብሮች አማካኝነት የሚከናወኑ የዶሮ እርባታ ምርታማነት በከፍተኛ መጠን እንዲጨምር ማድረጉን፤ የእንቁላል ገበያም እንዲረጋጋም የዶሮ በሽታ መጠን እንዲቀንስ መደረጉ አስተዋፅዖው የላቀ እንደሆነ ነው ያስረዱት።

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ፤ ኢንስቲትዩቱ ነባርና ባሕላዊው እውቀቶችን ከዘመናዊ የምርምር ሥራዎች ጋር በማጣመር፤ በመቀመር ያወጣቸው ስድስቱም አዳዲስ የእንስሳት መድኃኒቶች የተለያዩ የምርምር ሂደቶችን እንዲያልፉ ተደርገዋል። መድኃኒቶቹ ፈዋሽነታቸው በሳይንሳዊ መንገድ ተረጋግጦ የወጡ ሲሆን በተጨማሪም በእንስሳት ላይ ተሞክረው ተረጋግጧል። በተጨማሪም በሃገሪቱ ከፍተኛ ተመራማሪዎች ምክረሃሳብ የተደገፉ ናቸው።

ከውጭ ከሚገቡት ጋር የንፅፅር ሥራም መሠራቱን ቢክሲሳ (ዶ/ር) አመልክተው፤ ‹‹እነዚህ መድኃኒቶች ለገበያ ከመቅረባቸው በፊት ከኢንስቲትዩቱ ባሻገር በሚመለከታቸው ተቋማት በፍተሻ ተረጋግጠው የእውቅና ሰርተፊኬት እንዲያገኙ ተደርጓል›› በማለት ተናግረዋል። በመሆኑም መድኃኒቶችን የማባዛቱ ሥራ በሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።

‹‹በተለይም እነዚህ የእኛ ግኝቶች ሃገሪቱ ለእንስሳት ሕክምና አሁን እያወጣች ያለችውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚታደግ በመሆኑ ወደ ፋርማስቲካል ኢንዱስትሪ መሄድ አለባቸው። የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ይህንን ግብዓት ቢጠቀሙ ከውጭ የሚገባውን መተካት ይቻላል›› ሲሉም ያስገነዝባሉ። በሌላ በኩል መድኃኒታማ እፅዋቶችን የማባዛት ሥራም ለወጣቶች የሥራ ዕድል እንደሚፍጥር ጠቅሰው፣ ወጣቶች እንዲደራጁና ከምርምር ማዕከሉ ጋር ትስስር በመፍጠር እንዲሠሩ ማድረግ እንደሚገባም ተናግረዋል።

እንደ ቢክሲሳ (ዶ/ር) ማብራሪያ፤ በተለይ የግሉ ዘርፍ በተቋማት የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎችን በመደገፍ የእንስሳት ሃብቱን ምርትና ምርታማነት ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህንን ማድረግ ከተቻለ ሃገሪቱ ካላት ሰፊ የእንስሳት ሃብት በተጨባጭ ተጠቃሚ እንድትሆን ያደርጋታል። በተለይም ከውጭ የሚገባውን መድኃኒት በሃገር ውስጥ በመተካት በአሁኑ ወቅት ለእንስሳት መድኃኒት የምታወጣውን የውጭ ምንዛሪ ማዳንም ይገባል። ይህ ሲሆን ደግሞ እንደሃገር ለተጀመረው የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ሁለንተናዊ ጥረት ስኬታማ ይሆናል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የልዩ ፍላጎት ስኬትና የማታ ትምህርት ድክመት

**አስናቀ ፀጋዬ**

በትምህርቱ ሴክተር ትኩረት ተነፍጓቸው ከቆዩ የትምህርት ዘርፎች ውስጥ አንዱ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ነው። እንዲያ ሲባል ግን በየዘመኑ በመጡ መንግሥታት በልዩ ፍላጎት ትምህርት ላይ ምንም ሥራ አልተሠራም ማለት አይደለም ። ነገር ግን በዚህ ትምህርት ዘርፍ ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት የጀመረው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው። ከመንግሥት ለውጥ በፊት በልዩ ፍላጎት ትምህርት ላይ የተሠሩ ሥራዎች አበረታች የነበሩ ቢሆንም አዲሱ የለውጥ መንግሥት ከመጣ ወዲህ ሥራዎቹ ተጠናክረው በመሠራታቸው በብዙ መልኩ ለውጦች መጥተዋል።

በተለይ ትምህርት ቤቶች ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች አመቺ ሆነውና ለነሱ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን በመሟላታቸው ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ ማሳለጥ ተችሏል። በልዩ ፍላጎት ትምህርት ላይ የሚፈለገው ውጤት ስለመጣም ነው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባዔውን ባደረገበት ወቅት ይህንኑ የመሰከሩት።

በሌላ በኩል ደግሞ በደርግ ዘመንም ይሁን በኢሕአዴግ ከመደበኛው ትምህርት ባልተናነሰ መልኩ ለማታ ትምህርት ትኩረት ተሰጥቶ በመሠራቱ ጥሩ ለውጥ መጥቷል። በማታ ትምህርት ዘርፍ ትኩረት በመደረጉ በተለይ በቀኑ ክፍለጊዜ ለመማር የማይመቻቸውና ጊዜያቸውን በሥራ ለሚያሳልፉ ዜጎች ራሳቸውን በትምህርት እንዲለውጡ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። በዚህም ቀላል የማይባሉ ዜጎች ቀን እየሠሩ ማታ እየተማሩ ራሳቸውንና ኑሯቸውን ማሻሻል ችለዋል ።

ከመንግሥት ለውጥ በኋላ ምንም እንኳን በማታ ትምህርት ላይ የተሠሩ ሥራዎች ቢኖሩም በሚጠበቀው ልክ ባለመሆኑ በተለይ በዚህ ዓመት አፈፃፀሙ ደካማ ሆኖ ተመዝግቧል። ይህንንም የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) የከተማ አስተዳደሩ የ2016 ዓ.ም የትምህርት ዘርፍ አፈፃፀም በቀረበበት ወቅት አረጋግጠዋል። በመደበኛው ትምህርት የተሠራውን ያህል ሥራ በማታውም መደገም እንዳለበት አፅንዖት ሰጥተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባዔውን በዚህ ሳምንት መጨረሻ አካሂዷል። በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም በሚገኘው የምክር ቤቱ መሰብሰቢያ አዳራሽ ለሁለት ቀናት በተካሄደው በዚህ ጉባኤ የምክር ቤቱ አባላት፣ አስፈጻሚ አካላት እና ጥሪ የተደረገላቸው ባለድርሻ አካላት ተገኝተዋል። በጉባኤውም የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸምና የ2017 ዕቅድ ላይ ውይይቶች ተደርገዋል። ውይይት ከተደረገባቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ ትምህርት ሲሆን በዚህ ዘርፍ በ2016 ዓ.ም የተከናወኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች በሪፖርት ቀርበዋል።

ከአዲስ አበባ ትምህርት ዘርፍ ጋር በተገናኘ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀረቡት ከንቲባ አዳነች አቤቤ በመዲናዋ በሁሉም ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት ትምህርትን በማስፋፋት የተማሪዎችን ቅበላ ከዕቅድ በላይ ማሳካት መቻሉን ተናግረዋል። በሁሉም ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት ትምህርትን በማስፋፋት የተማሪዎችን ቅበላ ከዕቅድ በላይ ማድረስ የተቻለው በአዲስ አበባ ከተማ የትምህርት ፍትሐዊነትን ለማስፈን በተደረገው ጥረት መሆኑንም ከንቲባዋ ጠቁመዋል።

በዚሁ የማጠቃለያ ጉባኤ ከንቲባ አዳነች አቤቤ የከተማ አስተዳደሩን የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምን አቅርበዋል። ከንቲባዋ በሪፖርታቸው የትምህርት ተሳትፎ፣ ፍትሐዊነት እና ጥራትን በማሳደግ በዕውቀት እና በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድን ለማፍራት በተሠራው ሥራ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላን ከ291 ሺ. 392 ወደ 316 ሺህ 931 ማድረስ መቻሉን ገልጸዋል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቅበላን በተመለከተ ደግሞ ቅበላውን 626 ሺህ 647 ማድረስ መቻሉን እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ9 እስከ 12ኛ ክፍል ቅበላን 232 ሺህ 30 ማድረስ መቻሉን ተናግረዋል።



ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፤



ዘላለም ሙላቱ(ዶ/ር)፤

በበጀት ዓመቱ የትምህርት ቅበላ ሥራውን 1 ሚሊዮን 175 ሺህ 608 አድርሰናል ያሉት ከንቲባዋ፤ የትምህርት ፍትሐዊነትን ለማስፈን በተደረገው ጥረት በሁሉም ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት ትምህርትን በማስፋፋት የተማሪዎችን ቁጥር 39 ሺህ 640 ማድረስ መቻሉን አስታውቀዋል። ትምህርት ቤቶች ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች አመቺ እንዲሆኑ ለማድረግ በ52 ትምህርት ቤቶች ራምፕ ጥገና እና ራምፕ በሌላቸው 15 ትምህርት ቤቶች በአዲስ መልክ የመገንባት ሥራ መሠራቱንም አመልክተዋል።

የትምህርት ቤቶችን መሠረተ ልማት ለማሻሻል በ"ትምህርት ለትውልድ" ንቅናቄ በገንዘብ 360 ሚሊዮን ብር፣ በግብዓት 5 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር፣ በጉልበት 154 ሚሊዮን 596 ሺህ 195 ብር እና በዕውቀት 99 ሚሊዮን 384 ሺህ 667 ብር በአጠቃላይ ከ6 ነጥብ 44 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ሀብት ማሰባሰብ መቻሉንም አብራርተዋል።

በተሰበሰበው ሀብትም የትምህርት ቤቶችን ደረጃ በማሻሻል እና በተማሪዎች ምገባ 779 ሺህ 231 በላይ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ እንዲመገቡ የተደረገ መደረጉን እና የተማሪ ዩኒፎርም፣ የትምህርት ቁሳቁስ እና የመምህራን ጋዋን ማቅረብ መቻሉን ከንቲባዋ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል በመደበኛው የቀን ትምህርት የተመዘገበውን ውጤት በማታው መርሐ-ግብር ለመድገም ሁሉም በትብብር ሊሠራ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) ገልፀዋል። ኃላፊው ይህን ያሉት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት እያካሄደ ባለው 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባኤ በቀረበው ሪፖርት ላይ የምክር ቤት አባላት ላነሱት ጥያቄዎች እና አስተያየቶች መልስ ሲሰጡ ነው።

ትምህርትን በተመለከተ በተነሱ ጥያቄዎች ዙሪያ ማብራሪያ የሰጡት የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር)ዘርፉ የብዙ ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸው፣ ተደራሽነት እና ጥራት ላይ ለውጥ ለማምጣት ከወትሮው በተለየ መልኩ ጠንካራ ሲሠራ እንደነበር ተናግረዋል። በከተማዋ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ከተተገበረ ጀምሮ የመጽሐፍት ኅትመት ትልቅ በጀት የጠየቀ እንደነበር አስታውሰው፤ በዚህም እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች 1 ለ 1 መጽሐፍት ማዳረስ መቻሉን ጠቁመዋል። ይህም ለትምህርት ጥራት ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል ብለዋል።

የተማሪዎች የመማሪያ ክፍሎች በተለይም የተማሪ ክፍል ጥምርታን ለማስተካከል «በትምህርት ለትውልድ» እንቅስቃሴ እና በከተማ አስተዳደሩ ልዩ ትኩረት መማሪያ ክፍሎች ተገንብተው የተጨናነቁ ትምህርት ቤቶችን የማስተካከል ሥራ መሠራቱንም አስረድተዋል። ከተማ አስተዳደሩ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በታችኛው እርከን ላይ በልዩ ትኩረት እየሠራ መሆኑንም አንስተው፤ ባለፈው ሳምንት ይፋ የሆነው የ8ኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተና ውጤት ይህንን ያመላክታል ብለዋል።

> **የማታ ትምህርት ላይ በቂ ሥራ ባለመሠራቱ አፈፃፀሙ ደካማ ሆኖ ተመዝግቧልና ጠንካራ ሥራ በመሥራት በመደበኛው ትምህርት የተመዘገበውን ውጤት በማታው ትምህርት መድገም ያስፈልጋል**

በዘንድሮው ዓመት የ8ኛ ክፍል ፈተና ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል 79 በመቶ የሚሆኑት 50 እና ከዚያ በላይ በማምጣት ወደ ቀጣዩ የክፍል እርከን ማለፋቸውንም ኃላፊው አስታውሰዋል። የተማሪዎችን ውጤት በተመለከተ ኃላፊው በሰጡት ማብራሪያ የ8ኛ ክፍል የቀን የመንግሥት ተማሪዎች 50 እና ከዚያ በላይ ያመጡት 82 ነጥብ 4 በመቶ ሲሆኑ የቀን የግል ትምህርት ቤት 96 በመቶ የሚሆኑ ተማሪዎች 50 እና ከዚያ በላይ በማምጣት ማለፋቸውን ገልጸዋል። በዚህም በድምሩ 87 ነጥብ 7 በመቶ የሚሆኑ ተማሪዎች ወደ ሚቀጥለው የትምህርት እርከን አልፈዋል ብለዋል።

በሌላ በኩል የ8ኛ ክፍል የማታ ተማሪዎች በጣም አነስተኛ ውጤት ማሳየታቸውን ኃላፊው ጠቁመዋል። የመንግሥት የማታ ተማሪዎች 16 ነጥብ 7 በመቶ ብቻ 50 እና ከዚያ በላይ የማለፊያ ነጥብ ያስመዘገቡ ሲሆን የግል የማታ ተማሪዎች ደግሞ 6 ነጥብ 7 በመቶ ብቻ ማለፋቸውን አንስተዋል። እንዲሁም በርቀት የ8ኛ ክፍል ከተማ አቀፍ ፈተና 5 በመቶ ተማሪዎች ብቻ ወደ ቀጣዩ ክፍል ማለፋቸውን ተናግረዋል።

በመደበኛ የቀን ትምህርት የተመዘገበውን ውጤት በማታው የትምህርት መርሐ-ግብር ለመድገም በልዩ ትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ ያነሱት ኃላፊው ለዚህም ሁሉም ሊረባረብ ይገባል ብለዋል። በውጤት ብቻ ሳይሆን በሥነ-ምግባር የታነጸ ሁለንተናዊ ስብዕና ያለው ትውልድ ለመገንባት ትምህርት ቤቶች ከአዋኪ ድርጊቶች ነፃ እንዲሆኑ በተሠሩ ሥራዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል መታየቱንም ኃላፊው አብራርተዋል።

ከዚህ አንፃር የከተማ አስተዳደሩ በቅድሚያ በልዩ ፍላጎት ትምህርት የመጣውን ለውጥ አጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል። በዚህ ትምህርት ዘርፍ ለውጥ ስለመጣ ሁሉም ነገር ተስተካክሎ አልቋል ማለት ስላልሆነ ቀሪ ክፍቶችን በማረምና ተጨማሪ ሥራዎችን በመሥራት የመጣውን ለውጥ ይበልጥ እንደሚያስጠብቅ ይገመታል።

ከዚህ ባለፈ የማታ ትምህርት ላይ በቂ ሥራ ባለመሠራቱ አፈፃፀሙ ደካማ ሆኖ ተመዝግቧልና ጠንካራ ሥራ በመሥራት በመደበኛው ትምህርት የተመዘገበውን ውጤት በማታው ትምህርት መድገም ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ከወረዳ እስከከተማ ድረስ ያለው የትምህርት መዋቅርና አመራር ሥራውን በኃላፊነትና በጥንካሬ እንደሚሠራ ይጠበቃል።

በልዩ ፍላጎት ትምህርት ላይ የመጣው ለውጥ እንዳለ ሆኖ ከአምናው ትምህርት በመውሰድ የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ውጤትን ለማማሻሻል ዘንድሮ ጠንካራ ሥራዎች ከወላጅ ጀምሮ እስከፍተኛ የትምህርት ሚኒስቴር ድረስ ሥራዎች ተሠርተዋል። ከዚህ አንፃር በሀገር አቀፍ የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ጥሩ ውጤት ይመዘገባል ተብሎ ይጠበቃል። የትምህርት ጥራትንና መሠረተ ልማትን ለማሻሻልም በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል። የዛኑ ያህል ውጤት ያልመጣባቸው ሌሎች የትምህርት ዘርፎች አሉና በነዚህ ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ ይጠበቃል።

# ወቅታዊ

# “የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ሀብት የሚፈስበት ብቻ ሳይሆን የሚታፈስበትም ይሆናል”

**ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል**
**የሥራና ክህሎት ሚኒስትር**



ፎቶ፡- ሳሙኤል ተስፋዬ

**ከሁለት ሺህ የሚልቁ ተቋማት የተፈጠሩለት ዘርፍ ነው። ከ100 በላይ የሚሆኑቱ ደግሞ በፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ደረጃ ዘምነዋል። ሦስት ሚሊዮን የሚጠጉ ሠልጣኞች በተቋማቱ ውስጥ በተለያዩ ደረጃ ሥልጠና ላይ ናቸው። ዘርፉ ከፍተኛ ሀብት የሚፈስበት ሆኗል። የነገዋ ኢትዮጵያ ከዚህም ዘርፍ በሚወጡ የሠለጠኑ እጆች የምትሠራ ሆናለች። የመንግሥት ዘርፉን የማጠናከር ቁርጠኝነትም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት እስከማቋቋም ድረስ ዘልቋል። ይህ ዘርፍ ብዙዎች ትኩረት ያልሰጡት ነገር ግን ብዙ ሚሊዮኖች እየፈሩበት ያለው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ነው።**

**ስመሆኑ መንግሥት ይሄንን ሁነኛ ዘርፍ ለማጠናከርና እንደ ጀርመን ያሉ ሀገራት ከደረሱበት ከፍታ ለማድረስ ምን እየሠራ ይሆን?፤ ፖሊሲዎቻችንና ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት በእርግጥስ ወደሚፈለገው ደረጃ ማድረስ የሚያስችሉ ናቸው? እነዚህና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች የቀረበላቸው የሥራና ክህሎት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ሙፈሪሃት ካሚል ዘርዘር ያለ ምላሽ ሰጥተውበታል። የሚኒስትሯ ሙሉ ቃለ ምልልስም እንዲህ ቀርቧል።**

**አዲስ ዘመን፡- የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና አንጻር ያሉት ተልዕኮዎች ምን እንደሆኑ ቢያብራሩልን?**

**ወ/ሮ ሙፈሪሃት፡-** የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን ከቴክኒክና ሙያ ዘርፍ አንጻር በጣም ወሳኝ ተልዕኮ ነው ያለው። ይሄ ተልዕኮ አንድን ኢኮኖሚ ተወዳዳሪ የማድረግ ተልዕኮ ነው። መነሻው የኢኮኖሚ ተወዳዳሪነት ቢሆንም እኛ ደግሞ የለየናቸው ጉዳዮች አሉ። የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ እንዲኖር በማድረግ ረገድ የራሱ የሆነ የማይተካ ድርሻ አለው። በሁለተኛ ደረጃም ማኅበራዊ ሁኔታዎቻችን የተሻሉና የጎለበቱ እንዲሆኑ ትልቅ ሚና እንዳለው ተመልክተናል። ዜጎችን የማስቻል ሁኔታውም ትልቅ ነው። በተለምዶ ማብቃት የሚባለው ማለት ነው። አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ ክህሎትም እውቀትም ካለው በራሱ የመተማመኑና ብቃቱ ያደገ ይሆናል። ስለዚህ ይሄንን ተልዕኮ የመወጣት ኃላፊነት አለብን።

**አዲስ ዘመን ፡- ስጠቀሷቸው ተልዕኮዎች መሳካት ምን ያህል ምቹ ፖሊሲ አለ ማለት ይቻላል**

**ወ/ሮ ሙፈሪሃት፡-** በፖሊሲ ደረጃ በቅርብ ጊዜ የወጣው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ የላቀ ግልጽነት ያለው ሆኗል። የሰው ኃይላችንን ለሀገር ውስጥም ይሁን ለዓለም አቀፍ ገበያ ብቁ አድርጎ ማዘጋጀት የሚያስችል እንደሆነም ማየት ይቻላል። ይሄም ብቻ አይደለም። ሀገር በቀል ለሆኑ እውቀቶችና ክህሎቶች ቦታ የሰጠ ፖሊሲ ነው። ከአሁን ቀደም በነበረው አካሄድ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፉ የሚታወቀው አነስተኛና መካከለኛ ሙያተኞችን ብቻ የሚያወጣ ዘርፍ ተደርጎ ነበር። ነገር ግን አዲሱ የቴክኒክና ሙያ ፖሊሲ ዘርፉ የላቀ የብቃት ደረጃን የሚያጎናጽፍ እንዲሆን ተደርጎ እስከ ደረጃ 8 ድረስ ያደገ እንዲሆን ተደርጓል። በአጭር ጊዜ በተለይ ሪፎርሙን ተከትሎ የተከናወኑ ሥራዎች ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት ትልቅ ሊባል የሚችል ነው። ወደተሻለ ደረጃም ለማድረስ የሚያስችል እንደሆነ መመልከት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን ፡- ዘርፉ በርካታ የሰው ኃይል ያለበት፣ በመንግሥት በኩልም ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት ሳቅ ያለ እንደሆነ ተገልጿል። ስመሆኑ በዚህ ደረጃ ትኩረት ያገኘው ይህ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውና እንዲኖረው የሚፈለገው ድርሻ እንዴት ይገለጻል?**

**ወ/ሮ ሙፈሪሃት፡-** ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ኢኮኖሚው ተወዳዳሪ እንዲሆን የማስቻል ተልዕኮ አለው ስንል አንድም በዘርፉ በእያንዳንዱ ንዑስ ዘርፍ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲኖረው በማድረግ ረገድ የማይተካ ሚና አለው ማለታችን ነው። በሁለተኛ ደረጃ በቴክኖሎጂ ሽግግር ያለው ሚና ተጠቃሽ ነው። ጠቅለል ተደርጎ የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ወይንም ተቋማት በኢኮኖሚው ውስጥ ያላቸው ዐቢይ ሚና ምንድን ነው ተብሎ ቢጠየቅ፤ አንደኛው የሚሆነው የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት ነው። ሌላኛው ደግሞ የቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ መሥራት ነው። ለምሳሌ በ10 ዓመቱ የፍኖተ ብልጽግና ላይ የቅድሚያ ቅድሚያ የተሰጣቸው አምስት ዘርፎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው ግብርና ነው። የግብርናው ዘርፍ ተለምዷዊ በሆነ መንገድ በምንሠራው ሥራ የምንፈልገውን ሽግግር ማረጋገጥ አንችልም። ስለዚህ ነባሩን የሰው ኃይል፣ ተለምዷዊ በሆነ መንገድ ሥራ ሲሠራ የቆየውን አርሶ አደር፣ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን እንዲሁም አዳዲስ ወደ ዘርፉ መግባት የሚፈልጉ ዜጎችንና ኩባንያዎችን ለዘርፉ ብቁ የሆነ ክህሎት ያላቸው እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ትልቅ አቅም አላቸው።

በፌዴራል ደረጃ አምስት ለሚኒስቴሩ ተጠሪ የሆኑ የግብርና ኮሌጆች አሉን። እነዚህ ኮሌጆች የግብርናውን ዘርፍ የሰው ኃይል ፍላጎት የሚያሟሉ ናቸው። በእነዚህ ብቻ አንቆምም በክልል ደረጃም ለየክልሎቹ ተጠሪ የሆኑ 20 አካባቢ የግብርና ኮሌጆች አሉን። እነዚህ ኮሌጆችም በየአካባቢው የሠለጠነ የሰው ኃይል እንዲያፈሩ ይጠበቃል። አሁን ላይ ማሠልጠን ብቻ ሳይሆን የመመዘንም ሥራ እየሠራን ነው ያለነው። ማሠልጠን ማብቃትና መመዘን ማለቴ ነው። የምዘና ሥርዓቱ ላይ ለምሳሌ መመዘን የሚፈልጉ አርሶ አደሮችን እየመዘንን ነው ያለነው። ምዘና የሚጠቅመው ተመዛኞች የት ደረጃ ላይ ነው ያሉት ምን ይጎድላቸዋል የሚለውን ለመለየትና ቀጣይነት ያለው የማብቃት ሥራ ለመሥራት ነው። ይሄ የግብርና ዘርፉን ትራንስፎርሜሽን መሠረታዊ የሚባል ለውጥ እንዲያመጣ ካለው እምቅ አቅምም አንጻር ትርጉም ያለው ሚና ይጫወታል ማለት ነው።

አሁን እኛ እያየን ያለነው ይሄንን ጉዳይ እንዴት አድርገን በብቃትና በፍጥነት እንሂድበት የሚለውን ነው። ምክንያቱም ትልቅ ቁጥር ያለው የኅብረተሰብ ክፍል ነው በግብርናው ዘርፍ ተሰማርቶ የሚገኘው።

**አዲስ ዘመን ፡- ከሪፎርም አንጻር በዘርፉ ምን እየተሠራ ነው?**

**ወ/ሮ ሙፈሪሃት፡-** በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ሰፊ የሪፎርም ሥራዎች ናቸው እየተሠሩ ያሉት። ክህሎት ማሻሻል ያስችላሉ ያልናቸውን 11 አካባቢ የሪፎርም መስኮች ተመርጠው ሥራዎች እየተሠራባቸው ይገኛል። አንዱ የሥልጠና ፍላጎት መር እናድርገው የሚል ነው። ፍላጎት መር እናድርግ ስንል ከአምስቱ የቅድሚያ ቅድሚያ ከተሰጣቸው ዘርፎች አንፃር የመቃኘት ሌላም ገበያ የሚፈልጋቸው ዘርፎች ካሉ እያየን እንሂድ የሚል ነው። ስለዚህ አንዱ ለግብርናው ከሰጠነው ትኩረት ጋር ይያያዛል።

በአምራች ዘርፉም (ማኑፋክቸሪንግ) በተለይም በኮንስትራክሽን፣ በቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ በጨርቃጨርቅ እና በግብርና ማቀነባበሪያ ላይ በትኩረት እየተሠራባቸው ያሉ ጉዳዮች አሉ። ሥርዓተ ትምህርቶቻችንም ይሁኑ ማሠልጠኛ መሣሪያዎቻችን ለወቅቱ በሚሆን ደረጃ የመከለስ ሥራ ሠርተናል። ተጨማሪ በሚያስፈልጉ ዘርፎች ላይ ደግሞ የግሉ ዘርፍና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት አሳትፈን አዳዲስ ሥርዓተ ትምህርት የማዘጋጀት ሥራ ሠርተናል። በዚህም ከ140 በላይ የሆኑ ሥርዓተ ትምህርቶችን በአዲስ መልክ የማዘጋጀት ሥራ ተሠርቷል። አብሮ ደግሞ ግን ለጎን የማሠልጠኛ መሣሪያዎችን የማዘጋጀት ሥራ ተሠርቷል ይህም በየጊዜው ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

ቱሪዝምን ካየን ደግሞ ይህም እንደ ዘርፍ ትልቅ አቅም ተደርጎ የተለየ ነው። ይህንን ዘርፍ ለማዘመን የቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተጠሪ ሆኗል። ለቱሪዝም ማሠልጠኛ ኢንስቲትዩት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ለቱሪዝም ዘርፉ የሰጠችውን ትኩረት የዋጀ የሥርዓተ ትምህርት ቀረፃ ሥራ ተሠርቷል። ከግል ዘርፉ ጋርም ከመቼውም በላይ ተቀራርበን ለመሥራት እየሞከርን ነው። በቱሪዝም የሙያ ዘርፍ ሥልጠናው እስከ ደረጃ ስምንት ድረስ ይሄዳል። በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ደረጃ ስምንት ማለት በተለምዶ የትምህርት ሥርዓት ፒኤችዲ የሚባለው ነው። ደረጃ ሰባት ደግሞ የማስተርስ፤ ደረጃ ስድስት የመጀመሪያ ዲግሪ ማለት ነው። ዘርፉ በየደረጃው እና በየእርከኑ በቂና ብቃት ያለው የሠለጠነ የሰው ኃይል በማዘጋጀት ረገድ ትልቅ ትርጉም ያለው አካሄድ ነው።

የቱሪዝም ዘርፉ ላይ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን አነሳሽነት የለሙ የቱሪስት መዳረሻዎችን ጨምሮ በአጠቃላይ የመስተንግዶ ኢንዱስትሪ የሚባለው ዘርፍ ላይ ሆቴሎች ላይ የሚሰማራውን የሰው ኃይልን ጨምሮ የማሠልጠን እና የማዘጋጀት ሥራን እየሠራን ነው ያለነው። ይህም እንደ ሀገር የቅድሚያ ቅድሚያ ከሰጠናቸው ዘርፎች ውስጥ የቱሪዝም ዘርፉ ትልቅ አበርክቶ ይኖረዋል ማለት ነው። በአጠቃላይ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎችን ታሳቢ ያደረገ የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራትም እየሠራን ነው።

ሌላኛው የማዕድን ዘርፉ ነው። የማዕድን ዘርፉ የቅድሚያ ቅድሚያ ከተሰጣቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው። የማዕድን ዘርፉ ለውጡን ተከትሎ ነው በዚህ ደረጃ ግልፅ በሆነ ፖሊሲ የተደገፈው። ስለዚህ ዝግጅት ይፈልጋል ማለት ነው። አንዱ ቅድም ያነሳሁት ፍላጎት መር የሆነ የክህሎት ልማት ሥራ ነው የምንሠራው ብለን ከአስራ አንዱ ሪፎርሞች አንዱ አድርገን ወስደነዋል። ልክ እንደዛው ሁሉ የየአካባቢውን የመልማት ፀጋን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ሥርዓት አደረጃጀት ነው የፈጠርነው። በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ውስጥ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ተቋማት ማዕከላት እየተባሉ ይለያሉ። ፖሊቴክኒኮች ላቅ ያለ እርከን ያላቸው ናቸው። 110 የሚሆኑ ፖሊቴክኒኮች አሉን። ፖሊቴክኒኮች በየአካባቢው አንፃራዊ ጠቀሜታ ላይ የተመሠረተ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና እንዲሰጡ በሚያስችል አደረጃጀት ነው የተዋቀሩት። ለምሳሌ የተሻለ የቱሪዝም ሀብት ልማት ያለበት አካባቢ ላይ ያሉ ኮሌጆቻችን ከቱሪዝም ሀብት ልማት ጋር የተያያዙ ሙያዎች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ ማለት ነው። የግብርና ሥራዎች የተሻለ ጠቀሜታ ያለው አካባቢ ከሆነ ደግሞ ግብርና እና ግብርና ነክ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር ትኩረት ያደርጋሉ ማለት ነው። ስለዚህ የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋማት ካሉበት አካባቢ ሀብትና ፀጋ ጋር በጥልቅ የተቆራኙ እንዲሆኑ ይደረጋል ማለት ነው። ይሄ አካሄድ የየአካባቢውን አለኝታ በደንብ አድርጎ ለማውጣት ያስችላል። ኢኮኖሚያችንም የተሳሰረ ሆኖ እንዲገነባ ነው የሚፈለገው። የመወዳደር አቅማችንን ያሳድገዋል።

ለማደግና ለመለወጥ ወሳኙና አንዱ የሰው ሀብት ነው። የሰው ሀብት ልማቱን ከነባራዊ ሁኔታ ጋር በተናበበ መንገድ ማዘጋጀት ከተቻለ በአንድ በኩል ጥራት ያለው ዝግጅት ለማድረግ ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ የየአካባቢውን የመልማት ፀጋ ወቅታዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚነት እንዲኖር ያግዛል። ካለን ነገር ጀምረን ማልማት ስንችል በአካባቢው ላይ ያለው ጥቅም ላይ ሳይውል ቀርቶ የነበረው ሀብት መልማት ይጀምራል። ያ ደግሞ አካባቢውንም ኅብረተሰቡንም ተጠቃሚ ያደርጋል። በተመሳሳይ በአይሲቲ በኩልም እየተሠሩ ያሉ በርካታ ሥራዎች አሉ።

የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ዘርፉ በቴክኖሎጂ የታገዘ አልነበረም። በኮቪድ ጊዜ ተጨባጭ ፈተና ሆኖ ታይቷል። ዩኒቨርሲቲዎች በተሻለ ፍጥነት እራሳቸውን ወደ ማስተካከል ሲገቡና የትምህርት ሥርዓቶቻችን በድረገጽ ለመስጠት ሲሞክሩ፤ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ግን እሱን ማድረግ አልቻሉም። ከተግባር ተምረን ሃያ የሚሆኑ የቴክኒክና ሙያ ተቋሞቻችንን የተሟላ መሠረተ ልማት እንዲኖራቸው አድርገናል። ለሌሎችም በዚሁ እንቀጥላለን። በዚህ ደረጃ እየተሠራ ነው። በቁጥር ካየነው የግሉንና የመንግሥትን ጨምረን ከአጭር ሥልጠና ጀምሮ የሚሰጡት ሁለት ሺ ገደማ እየተጠጉ ናቸው። ሁሉንም ደረጃ በደረጃ ወደዛ ማሸጋገር ይጠይቃል። አሁን ላይ እየሠራን ያለነው የፖሊቴክኒኮችን አቅም መገንባት ላይ ነው። የፖሊቴክኒኮቹ አቅማቸው ሲገነባ በእነሱ ዙሪያና በአካባቢያቸው ያሉ በኮሌጅ ደረጃ ያሉ ተቋማትን ይዘው ይወጣሉ የሚል የትስስር ሥርዓትም ጭምር ተዘርግቶላቸው ነው እየተሠራ ያለው። በዚህ መልኩ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# “የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ሀብት የሚፈስበት...

ከገጽ 9 የዞረ

የኢኮኖሚ እድገታችን የቅድሚያ ቅድሚያ ለሰጣቸው ዘርፎች የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓቱን አዘጋጅቶ ለመሄድ ጥረት እየተደረገ ነው ያለው።

**አዲስ ዘመን :- ከሪፎርም አንጻር ይሄንን ያህል ርቀት ከተሄደ፤ በመንግሥት በኩል ለዘርፉ ምን ያህል ሀብት እየተበጀተ ነው?**

**ወ/ሮ ሙፈሪሃት:-** ዘርፉ በባሕሪው ከፍተኛ ካፒታል የሚፈልግ ነው። ምክንያቱም ብዙ ማሽነሪዎችን ይፈልጋል፤ ብዙ ወርክሾፕ መኖር አለባቸው፤ ጊዜውን የዋጀ መሆንም አለባቸው። ውድድሩን እንደምታውቁት በጣም ጠንካራ ነው። የእኛ ኢኮኖሚ ያለውን እምቅ አቅም እንዲያወጣ ከተፈለገ እዚህ ዘርፍ ላይ የሚሠራው ሥራ ወሳኝ ነው። ካለው ቋት በመመደብ ረገድ ደረጃ በደረጃ እያደገ የመጣ የሀብት ድልድል አለ። ያለፉት ሁለት ዓመታት እንደ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከተቋቋምንበት ጊዜ ጀምሮ የሚደረጉ ጥረቶች አሉ፤ ነገር ግን ከአንድ ምንጭ ብቻ በሚገኝ ሀብት ይሄንን ዘርፍ ማሳደግ አይቻልም። በዚህም ምክንያት ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንከር ያለ ሥራ እንሠራለን። ቁጥራቸው ውስን ቢሆንም አቅድ ይዘን ስልት ነድፈን ባለድርሻ አካላቱን የማብዛትና የማስፋት ሥራ እየሠራን ነው ያለነው። በአንድ ቋት ሀብቶቹ እንዲሰባሰቡና ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው በዘርፉ ውስጥ ለተለዩ የለውጥ ሥራዎች እንዲውሉ የማድረግ ስልት ተከትለን እየሠራን ነው።

ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅርቡ መንግሥት ባደረገው ድርድር 200 ሚሊዮን ዶላር ከዓለም ባንክ በብድርም በእርዳታ መልክም ለማግኘት ጥረት ተደርጓል። የጀርመን ልማት ድርጅትም ዘርፉን ያግዛሉ። በቅርቡ ደግሞ የጣሊያን መንግሥትም ይሄን ዘርፍ ለማገዝ እየሠራ ነው። የአውሮፓ ኅብረትም መንገድ ላይ ነው ያለው። የመንግሥትን አቅም እና የልማት አጋሮቻችንን አቅም ተጠቅመን ነው እየሠራን ያለነው። እኛ ደግሞ እንደአቅጣጫ ይዘን እየሠራን ያለነው እራሳቸው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ሀብት የማመንጨት ዕድል አላቸውና ያንን ተጠቅመው ሃብት ማመንጨት አለባቸው የሚል ነው። የወርክሾፖቻችንን አቅም ብዙዎቹ ከሥልጠና በላይ ነው። በጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ የኢንዱስትሪ ደረጃ ላይ ያሉ ዘርፎች ሲቸገሩ እነሱን እያገዝን በትርፍ ሰዓት ደሞ ከሥራ ውጭ የሆኑ ማሽኖችን በትርፍ ዓይን ሳይሆን አገልግሎት በመስጠት ዓይን በሚገኝ ገቢ ራስን የመደጎም አቅጣጫ እንከተላለን። ይሄ ግን ዋና ተግባር አይሆንም።

በአጠቃላይ በእኛ እቅድ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት እራሳቸውን መቻል አለባቸው የሚል አቅጣጫ ነው ያለን። በዚያ መርሕ እየሠሩም ነው ያሉት። በሪፎርሙ ያስቀመጥነው አቅጣጫ ሠልጣኞች ወደ ተቋም ከገቡበት ጀምሮ ወጥተው ሥራ የሚፈልጉ ሳይሆኑ በቆይታቸው ሂደት ሥራ እንዴት እንደሚፈጠር ተለማምደው እራሳቸው ኩባንያ መሥርተው መውጣት አለባቸው፤ መመረቂያቸው ወረቀት ሳይሆን ኩባንያ መመሥረት መሆን አለበት የሚል ነው። እንደዚህ ሲሆን ሥራና የቴክኒክና ሙያ ሥርዓቱ የተሳሰረ ይሆናል ማለት ነው። ያንን ልምምድ ለመሥራት የፈጠርናቸው ኩባንያዎች በጣም ባጭር ጊዜ በ100 ሚሊዮኖች ብር የሚቆጠር የሥራ ትዕዛዝ ተቀብለው እየሠሩ ነው። የግብርና ኮሌጆቹም አግሮ ፕሮሰሲንግ ላይ ገብተዋል። ዘይት መጭመቅ፣ ማር ማምረት ጀምረዋል። የሐር ትል ልማት ላይም በስፋት ይሳተፋሉ። በጣም ቆንጆ ቆንጆ የሐር ምርት ውጤት የሆኑ አልባሳትን ማምረት ጀምረዋል።

በአጭር ጊዜ በተሠራው ሥራ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት አይተውት ሰምተውት የማያውቁትን የገንዘብ መጠን ማፍራት የቻሉበት ሁኔታ ውስጥ መግባት ጀምረዋል። የሁሉም የተጠቃለለ ሪፖርት ሲደርስ ማወቅ ይቻላል። ከላይ የጠቃቀስኳቸው ሥራዎች በተለይም በዚህኛው ዓመት ነው ተሟልቶ ወደ ሥራ እየገቡ ያሉት። ከእነዚህ ተቋሞቻችን በጀመሩት መንገድ ወደ ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ሀብት እንጠብቃለን። ይሄ ሆኖም ኖሮም አያውቅም። አዲስ አበባ ላይ ያሉ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትንም ብናይ ተመሳሳይ አዳዲስ ምርቶችን ማፍራት ጀምረዋል። ሥራዎችን ተቀብለው መሥራት ጀምረዋል ብሎ መውሰድ ይቻላል።



የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ምን አይነት አተያይ ነው ያለው የሚለውን ለማየት ሞክረን ነበር። የእኛ ማኅበረሰብ በመስማት ብቻ ሳይሆን በማየትም ጭምር የሚያምን ማኅበረሰብ ነው። ስለዚህ የቴክኒክና ሙያ ተቋማቱ “ሆነው እንዲገኙ” እናድርግ የሚለውን የመጀመሪያ አቅጣጫ አድርገን ነው የያዝነው። በተግባር ሆነን እንገኝ ብለን የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓቱን ከሥልጠና በላይ በሚል አጠቃላይ እሳቤ ተርጉመነዋል። ከሥልጠና በላይ ያልነውን ጉዳይ ወደ ተግባር ጠንቅቀን ወደ ሥራ እየቀየርን ስንሄድ የቴክኒክና ሙያ ተቋማቱ ሳቢ ይሆናሉ። ዋል አደር ያለውን አስተሳሰብ ለመቀየር በተጨባጭ እነዚህ ስፍራዎች ላይ የሚገኘውን ክህሎት እና እውቀት በፈለጉት ሰዓት የፈለጉትን ማድረግ የሚችሉ ወርቃማ እጅ ያላቸውን ሰዎች በመጠቀም እየሠራን ነው። ዜጎች ይሄ ገብቷቸው እንዲወስኑ ለማድረግ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት እንደ ዘርፍ የሚሰጡትን ጥቅም ማሳየት የሚያስችል ሥራዎችን እንሥራ በሚል እነዚህ ተቋማት ከሀሳብ እስከ ምርት እስከ ምስለ ምርት የሚሄድ ሥራ እየተሠራባቸው ነው ያለው።

የቀደመውን የተሳሳተ ግንዛቤ ለመቀየር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሚያደርገው ውትወታ ብቻ የተሟላ ግንዛቤ ማስያዝ አይቻልም። አንተም ያልከውን አይነት የተዛባ ትርክትና በቴክኒክና ሥልጠና ዘርፍ ያለውን አስተሳሰብ በተወሰነ ደረጃ መስበር ጀምረናል ማለት እችላለሁኝ። ለምሳሌ አምና ያስመረቅናቸው ልጆች የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት የነበራቸው ይሄንን ዘርፍ የመረጡና የሠለጠኑ ናቸው። ይሄ ዘርፉ ላይ ያለው የተዛባ ነገር እየተስተካከለ ነው ማለት ነው። የእኛ የኮሙኒኬሽን ሥራ ዋል አደር ያለውን ችግር በደንብ ለመቋቋም የሚያስችል እንዲሆን አድርጎ ከሚዲያ ጋር የነበረውን ሥራ ማጠናከር ይኖርብናል።

**አዲስ ዘመን:- በርካታ ተቋማት ከቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የተመረቁትን ለመቅጠር ፍላጎት አይታይባቸውም። ይሔ ተግዳሮት እንዴት ነው እየታለፈ ያለው ?**

**ወ/ሮ ሙፈሪሃት:-** ጥሩ ጥያቄ ነው። በግሉ ዘርፍ “ማሽን ይሰብራሉ፤ ማሽን ያበላሻሉ” የሚል ሪስክ ያለመውሰድ ጉዳዮች አሉ። ሁሉም የግል ዘርፍ ማለት ቢያስቸግርም ቀላል ባልሆነ ደረጃ እንደዛ አይነት ተግዳሮት አለ። እዛ አካባቢ ያለውን መረዳት ለማስተካከል እየጣርን ነው። ምክንያቱም ለጋራ ሀገር ኃላፊነት ተከፋፍሎ መሥራት ካልተቻለ ጥንቅቅ ያለ ያለቀ የሚባል ነገር የለም። ሰው በተግባር ሂደት ነው የሚገነባው። እዚህ ያገኘውን መሠረታዊ እውቀት ይዞ መግባት ሲችል ነው የሚገነባው። ይሄንን ችግር ለመሻገር አንዱ እየሠራን ያለነው ከግል ዘርፉ ጋር ተቀራርቦ መስራት ነው። ከንግድና ዘርፍ ማኅበራት ጋር የጀመርናቸው ሥራዎች አሉ።

በሥራ ዕድል ፈጠራ ዘርፍ የጀመርነው አንድ ሥራ አለ። ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓቱ ጋር አብሮ የሚዛመድ የሰው ኃይል አሠልጥነን ወጣቶችን ኢንዱስትሪዎች ጋር እናስገባቸዋለን። ለወራት እዛ ይለማመዳሉ፤ አፈጻጸማቸውን እያሻሻሉ እያስተካከሉ ይሔዳሉ። መጨረሻ ላይ ይቀጠራሉ። በዚህ መንገድ 11 ከተሞች ላይ የጀመርነው ፕሮጀክት አለን። ተቀጣሪ የሆኑበት ሁኔታም አለ። በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፉ ላይ ግን የተለየ ታሪክ ነው ያለው። ሠልጣኞች ሆቴሎች ጋር ሄደው ልምምድ ያደርጋሉ። ተመርቀው ከወጡ በኋላ ሳይሆን እስኪጨርሱ ሳይጠብቁም ይቀጠራሉ። በአንጻራዊነት በአገልግሎት ዘርፉ በኩል ያለው የተሻለ ነው። በማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ነው ቻሌንጅ ያለው፣ እሱን ደግሞ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣው ደንብ አለ። ይሄ ደንብ የተባለውን ትስስር የሚፈጠርበትን መንገድ የሚያመቻች ነው።

**አዲስ ዘመን :-በዘርፉ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የአሠልጣኞች ወይም የመምህራንን ብቃት እና ገቢያቸውንም ማሳደግ ወሳኝ ድርሻ አለውና ከዚህ አንጻር ምን እየተሠራ ነው?**

**ወ/ሮ ሙፈሪሃት:-** ይሄም አንዱ የሪፎርም አጀንዳ ነው። ቀደም ሲል የተካሄዱ ጥናቶች አሉ። ተጨማሪ ዳሰሳዎችንም አድርገን የደረስንበት እኛ የምንገኝበት ቴክኒክ እና ሙያ ሥልጠና ዘርፍ ሥርዓት እያደገ ያለ ቢሆንም ሃገራት ከሄዱበት ርቀት አኳያ የማካካሻ ሥራ የሚፈልጉ ጉዳዮች እንዳሉ ነው። እነዛን የማካካሻ ሥራዎች ለመሥራት የአሠልጣኙ ጉልበት እና ጥበብ በጣም ወሳኝ ነው ብለን ነው የተመለከትነው። የመልካም አስተዳደር ጉዳዮችም አሉ። የዋሉ ያደሩ አዳዲስም የተፈጠሩም ሊኖሩ ይችላሉ። ይሄንን ማስተካከል ይኖርብናል።

አሠልጣኙ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶችን መታጠቅ ያስፈልገዋል። የመምህራን የአሠለጣጠን ዘይቤ ኢኖቬቲቭ የሆነ ነው። የምንሠራው ሥራ በዛ ደረጃ ትርጉም ያለው መሆን አለበት በሚል የተቀረጹ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች አሉ። ክረምት ላይ ሰፋ ያለ ሥልጠና እንሰጣለን ብለን ዝግጅት እያደረግን ነው ያለነው።

ከዛ ባሻገር ግን በመደበኛው የሥልጠና ፕሮግራሞች የማስተርስ፣ የፒኤችዲ ፕሮግራሞችን ጨምሮ ወይም በእኛ የሌቭል 7 እና 8 በሃገር ውስጥም በውጭም የአመራር ክህሎት ሥልጠናዎችን እየሰጠን ነው። መምህራንም ከደረጃ ወደ ደረጃ ማሸጋገር የሌቭል ሲ፣ ሌቭል ቢ፣ ሌቭል ኤ የሚባሉ የሥልጠና ሥርዓቶች አሉ። ከአንዱ እርከን ወደ አንዱ እርከን የሚሸጋገሩበት የቆየ የሥልጠና ሥርዓት አለ፤ እርሱንም ተግባራዊ እያደረግን ነው ያለነው።

ከኑሮ አኳያ መሻሻል አለባቸው ብለን የለየናቸው ጉዳዮች አሉ። የመንግሥት ደሞዝ እየጠበቁ፣ የመንግሥት ማሻሻያ እርከን እየጠበቁ መኖር በዚህ ዘርፍ ነውር ነው መሆን ያለበት፤ ቅድም እንዳነሳሁት ሌሎች የሌላቸውን ዕድል ይህ ዘርፍ አለው። የእንጨት ሥራ አሠልጣኝ የሆነ ሰው ለምሳሌ በሚጨምረውና በምትጨምረው እሴት ልክ ወደ እራሱ የሚሄድ ነገር ማምጣት ያስፈልጋል። በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓት ውስጥ በደንብ እንዲጎለብት ማድረግ ያለብን እሴት እየጨመረ፣ ዘርፉንም እየጠቀመ እራሱንም እየጠቀመ የሚሄድበት ሥርዓት እንዲኖር ነው። የተጋ በትጋቱ ልክ የሚጠቀምበት ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ ጀምረናል። አዲስ አበባ ለምሳሌ ወረድ ብላችሁ ብታዩ አንዳንድ ኮሌጆች አስራ አንዱንም ዘረ መሎች ተግባራዊ አድርገዋል። በተቋም ደረጃ እንደ ዊንጌት ያሉ ተቋሞቻችን ዓለም አቀፍ ሰርተፍኬት አግኝተዋል። ከተቋም አልፎ ደግሞ ወደ ግለሰብ አሠልጣኞቻችን እናሳድጋለን። እነዚህ አሠልጣኞች በዚህ ደረጃ ሰርቲፋይድ ከሆኑ የትኛውም የዓለም ጫፍ ላይ ሄደው መሥራት ይችላሉ ማለት ነው። ወደዛ ነው እየወሰድን ያለነው። ይሄ ሥራ የመምህራንን የአሠልጣኞችን ተነሳሽነት ንቃት እና በሂደት ውስጥ ተጠቃሚነት ይበልጥ እያጎለበተ ይሄዳል። እንደ አንድ የትኩረት አቅጣጫ ተይዞ እየተሠራበት ነው ያለው። ሌሎችን ሲሠሩ ማውራት ይሻላል ። ሂደት ከምናገር ብዬ ነው።

**አዲስ ዘመን :- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናን ዘርፍ የዛሬ 10 ዓመት የት እንጠብቀው?**

**ወ/ሮ ሙፈሪሃት:-** ጥሩ ማሰብ ጥሩ መመኘት እና ጥሩ መተለም በጣም ጥሩ ነው። እነዚህ የተጀመሩ የሪፎርም ሥራዎች ሳይቆራረጡ በደንብ ከዳር መድረስ ከቻሉ ጨዋታ ለዋጭ የሆነ ዐሻራ ማኖር የሚችል ዘርፍ ነው ብዬ ነው የማስበው። በሰው ኃይልም ልማትም በቴክኖሎጂ ሽግግርም ኢትዮጵያን እንደ ሀገር በሁለት እግር የሚያቆሙ በርካታ ቴክኖሎጂዎች የሚወጡባቸው ማዕከላት ይሆናሉ። ብዙ ሚሊዮኖችን የሚለውጡና የሕይወት ትርጉም የሚሰጡ ማዕከላት ይሆናሉ። ዘርፉም እንደ ዘርፍ እንደዛ ይሆናል።

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እሴት ጨምሮ ተወዳዳሪ ሆኖ የሚወጣበትን ጉልበት የሚሰጥ ዘርፍ ይሆናል። በዚህ ሂደት ትርጉም ያላቸው ማኅበራዊ ኢኮኖሚያና ለፖለቲካዊ ስኬቶች እንዲሳኩ አስቻይም ዘርፍ ነው። እራሱ የዘርፉ ተቋማዊ ባሕሪ ማስቻል ነው። ግለሰብን ማስቻል፤ ቤተሰብን ማስቻል፤ ማኅበረሰብን ማስቻልና ተቋማትን ማስቻል ነውና። ይህን አስቻይነቱን በብቃት የተወጣ ዘርፍ መሆን ይችላል። ስለሆነም የኢትዮጵያ የእድገትና የመለወጥ ጉዞ ውስጥ ትርጉም ያለው አሻራ የሚያሳርፍ ዘርፍ ይሆናል። በአስር ዓመቱ በዚያ ደረጃ ልንጠብቀው እንችላለን። በአምስት ዓመት ውስጥ ደግሞ ዲጂታል ላይ ምን እናሳካለን ብለን ከወሰድን እራሳቸውን የቻሉ በራሳቸው ገቢ የሚተዳደሩ ለአሠልጣኞቻቸው ምቹ ሁኔታ የፈጠሩ ሠልጣኞቻቸውን ተወዳዳሪ ያደረጉ የተበራከቱ ተቋማት ማየት ይቻላል ብዬ ነው የማስበው።

**አዲስ ዘመን:- በመጨረሻም ያገናኘን የቴክኒክና ሙያ ሳምንት ነውና ለዘርፉ ተዋንያን የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ዕድሉን ልስጥዎት።**

**ወ/ሮ ሙፈሪሀት:-** መልካም እንግዲህ የዘርፉ ተዋንያን አንድም የገዘፈ ሚና ያላቸው መሆኑን ሁልጊዜ እንዲያስታውሱ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ሰዎች ዘርፉን ያስቀመጡት ቦታ ላይ ሳይሆን በዘርፉ ውስጥ የነቃ ሚና የሚጫወቱ አካላት ዘርፉ ውስጥ ያለውን ጉልበትና አቅም በደንብ ይገነዘባሉ ብዬ አምናለሁ። በጊዜያዊ የግንዛቤ ችግር ዘርፉን በተመለከተ የተለያየ አተያይና መረዳት ቢኖርም የዘርፉን እምቅ አቅም በማውጣት ረገድ ደግሞ ዘርፉ ውስጥ ያሉ ተዋንያን የማይተካ ድርሻ አላቸው። በግላቸውም እንደተቋምም ዘርፉ ውስጥ እንዳለ የቤተሰብ አባል የዘርፉን እምቅ አቅም በመግለጥ ሂደት ደከመን ሰለቸን ሳይሉ አዕምሯቸውን፣ ልቦናቸውንና ወርቅ እጃቸውን አስተሳስረው የሚሠሩትን ሥራ በላቀ ትጋትና ጥራት መሥራት እንዲችሉ አደራ ማለት እፈልጋለሁኝ። እናንተ ያያችሁትን ብርሃን ሁሉም እንዲያይ በማድረግ ረገድ በተግባር እንገለጥ የሚል መልዕክት ነው ያለኝ።

**አዲስ ዘመን :- ስለሰጡኝ ሰፋ ያለ ማብራሪያና ጊዜዎት እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።**

**ወ/ሮ ሙፈሪሃት:-** እኔም በጣም ነው የማመሰግነው።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ተፈጥሯዊ የፊት ቆዳ መጠበቂያ ምርቶች

**ሰሚራ በርሀ**

ዲክራ ሸኪብ ትባላለች። ዲክራ ተወልዳ ያደገችው በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል በድሬዳዋ ከተማ ነው። ተፈጥሯዊ ግብዓቶችን በመጠቀም ፊትን መንከባከብና ማስዋብ የሚያስችሉ የቆዳ መጠበቂያ ምርቶችን አዘጋጅታ ለገበያ እንደምታቀርብ ትናገራለች። ‹‹እኔ ባደግኩበት የምሥራቁ ክፍል በተፈጥሯዊ ግብዓቶች ቆዳን መንከባከብ የተለመደ ነው›› ስትል ጠቅሳ፣ ይህም ግብዓቶቹን ለማዘጋጀት መነሻ እንደሆናት ትገልጻለች።

የጉዞ አስጎብኚ ባለሙያ እንደነበረች ትናገራለች። ትዳር መሥርታ የልጆች እናት ስትሆን፣ ቤት ውስጥ በመሆን ልጆቿን ለማሳደግ ትወስናለች። ይህን ጊዜም በፌስቡክ የማኅበራዊ ገጽ ላይ በቤት ውስጥ ሆነው ልጆቻቸውን ለሚያሳድጉ እናቶች በተፈጥሯዊ ግብዓቶች እንዴት የፊታቸውን ቆዳ መንከባከብ እንደሚችሉ ልምዷን ማጋራት ውስጥ ገባች።

‹‹አብዛኛዎቹ ሴቶች ራሳቸውን መንከባከብ ይፈልጋሉ። ነገር ግን ግብዓቱን ከየት እንደሚያመጡት እና እንዴት ማዘጋጀት እንደሚጀምሩም አያውቁም›› የምትለው ዲክራ፤ እነዚህን ተፈጥሯዊ ግብዓቶች ከድሬዳዋ በማምጣት ከአራት ዓመት በፊት ቤቷ ውስጥ ማዘጋጀት መጀመሯን ታስታውሳለች።

እሷ እንዳለችው፤ በድሬዳዋ የፊት ቆዳን በመንከባከብ በኩል በስፋት የሚታወቀው ቀሲል ወይም የቆርቆራ ዛፍ ነው። ፍሬው የሚበላ ሲሆን፣ የቅጠሉ ዱቄት ደግሞ ከውሃ ጋር እንዲቀላቀል ይደረጋል፤ ይህን ጊዜም አረፋ ያወጣል፤ አረፋውም ሳሙናን በመተካት ፊትን ለመታጠብ፣ ቆዳን ለማፅዳት እንዲሁም ለፀጉር እንክብካቤ ይውላል።

‹‹ወደሀገር ውስጥ የሚገቡ የተለያዩ የቆዳ መጠበቂያ ምርቶች በገበያው ላይ ቢገኙም፣ የሶማሌ ሴቶች ግን ይህ ዕፅዋት ፊትን ለመንከባከብ በእጅጉ ይመርጡታል። ብዙዎች አሁን ተፈጥሯዊ መንከባከቢያዎችን ትተው



ዲክራ ሸኪብ

ለተለያዩ ኬሚካሎች እየተጋለጡ ነው›› ስትል ታብራራለች።

እሷ ግን ይህን ዕፅዋት ነው ለቆዳ መጠበቂያነት እንዲውል የምታደርገው። ይህን የማደርግበት ዋና ዓላማ ከውጭ ለሚመጡ ምርቶች የምናወጣውን ወጪ ለመቀነስ እና እየተረሳ የመጣውን በባሕላዊና ተፈጥሯዊ የቆዳ መጠበቂያ ዘዴ ለማስታወስ ነው›› ትላለች ።

በማኅበራዊ ገጽ ከተለያዩ እናቶች ጋር ልምድ በመለዋወጥ የጀመረችው ይህ ተፈጥሯዊ ፊት የመንከባከቢያ ዘዴ የማዘጋጀት ሥራ፣ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ መምጣቱን ነው የተናገረችው። ይህን ዘዴ የተጠቀሙ ብዙዎች ለውጥ ማየታቸውንም ትጠቅሳለች። ዲክራ የፊት መንከባከቢያ ምርቶች እንዴት ይዘጋጃሉ በሚል በበይነ መረብ የሚሰጡ ተከታታይ ትምህርቶችን በመከታተልም ልምዷን ማሳደግ ትላለች ።

አሁን ላይ ‹‹ዚክራ ናቹራል›› በሚል ስያሜ ከተፈጥሯዊ ግብዓቶች የሚዘጋጁ ከአራት በላይ የፊት ቆዳ መንከባከቢያ ምርቶችን እንደምታዘጋጅ ጠቁማለች። እነዚህም አንድ የፊቱን ቆዳ ለመንከባከብ የሚፈልግ ሰው ሊያውቃቸው የሚገቡ ግብዓቶች መሆናቸውን ጠቅሳለች። ‹‹ለፊታችን ከሚያስፈልጉን ምርቶች የመጀመሪያው ፊትን የሚያፀዳው ነው፣ ፊት ከፀዳ በኋላ ደግሞ ለቆዳችን እርጥበት የሚሰጥ ግብዓት ያስፈልገናል። ሌላው የፀሐይ መከላከያ ሲሆን፣ ከዚያም የፊታችንን ቆዳ ጥርት የሚያደርጉ ውሕዶችን መጠቀም እንችላለን ›› ስትል ታብራራለች።

ሳሙናን ተክቶ ፊትን ለማፅዳት የሚውለው ቀሲል፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ሌላ መጠሪያ እንዳለውም ዲክራ ትገልጻለች። ቀሲል በውስጡ የቫይታሚን ሲ ንጥረነገር እንዳለው ጠቅሳ፣ ፊትን የማፅዳት እና የማፍካት ባሕሪ እንዳለው ነው ያመለከተችው። ሌላኛው ምርት የጽጌሬዳ አበባ ውሃ መሆኑንም ጠቁማ፣ ይህ ውሃ ፊት እርጥበት እንዲኖረው እና በተለያዩ ባክቴሪያዎች አማካኝነት ፊታችን ላይ የሚወጡ እንከኖችን ለመከላከል ይጠቅማል ትላለች።

ዲክራ ከምታዘጋጃቸው የፊት መንከባከቢያ ውሕዶች ውስጥ ከሌሎች ውሕዶች ጋር ተቀይጦ የሚዘጋጀው በማዕድን የበለጸገ የሸክላ አፈር ይጠቀሳል፤ ይህን ግብዓት በመጠቀም በኩል ግብፅ፣ ሞሮኮ እና አንዳንድ የዓረብ ሀገራት በስፋት እንደሚጠቀሙበት ይጠቀሳል፤ ግብዓቱም ባሕርና ደለል ያለበት አካባቢ ይገኛል ።

እሷም ይህንን ምርት ከእነዚህ ሀገራት በማስመጣት ከሀገር ውስጥ ዕፅዋቶች ጋር በመደባለቅ ታዘጋጃለች። ‹‹በማዕድን የበለጸገ የሸክላ አፈር በሀገራችን ቢገኝም፣ ለፊት ቆዳ መንከባከቢያነት ለመዋል የተለያዩ ሂደቶችን ማለፍና በዘርፉ ባለሙያዎች ተመርምሮ መረጋገጥ እንደሚኖርበትም አስገንዝባለች።

የእርድ ውሕድም ታዘጋጃለች። ይህንን ግብዓት ብዙዎች ይጠቀሙበታል። ከተለያዩ ግብዓቶች ጋር በመደባለቅ ነው ውሕዱን የምታዘጋጀው። ውሕዱ በፀሐይ ለተጎዳ ፊት፣ ብጉር ላለባቸው ሰዎች እና ፊትን ለማፍካት ያገለግላል።

ፊትን ለማለስለስ የሚውለው የፊት ቅባትም ታዘጋጃለች። ይህንንም ከወይን ፍሬ ዘይት፣ ከአልመንድ ፍሬ እና ከሌሎች ግብዓቶች ነው የምታዘጋጀው። ቅባቱ ፊታችን ላይ የሚገኘውን ተፈጥሯዊ ወዝ የሚተካ መሆኑን ጠቅሳ፣ የተለያዩ ውሕዶችን ከተጠቀምን በኋላ ሊከሰት የሚችለውን ድርቀት ለመከላከል እንደሚጠቅመም ጠቁማለች።

ዲክራ በብዙዎች ዘንድ ተመራጭ የሆነውን ቀሲል 150 ግራም በ300 ብር እና 300 ግራም በ500 ብር ለገበያ ታቀርባለች። ይህም ለረጅም ጊዜ የሚያገለግል መሆኑን ጠቅሳ፣ በጥቅል መልክ የሚዘጋጀውን የቆዳ መንከባከቢያ ለደንበኞቿ የምታቀርበው በቆዳቸው አይነት ላይ ምክር ከሰጠች በኋላ መሆኑንም ትናገራለች። በጥቅሉ በሁለት ሺህ 200 ብር የሚሸጠው ግብዓት ለሦስት ወር ያህል እንደሚያገለግልም ገልጻለች።

ቀሲል በየእለቱ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችልና ውሕዶችን የያዘው ጥቅል ደግሞ በሳምንት ለሦስት ቀናት መወሰድ እንዳለበትም ተጠቃሚዎቿን ትመክራለች። የፊት መንከባከቢያዎቹ የሚያመጡት ለውጥ እንደየሰው የፊት ሁኔታ እንደሚለያየም ጠቅሳ፣ ከሁለት ሳምንት ጀምሮ እስከ ሦስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ግን ለውጥ እንደሚታይ ጠቁማለች።

ዲክራ አሁን ላይ በሀገር ውስጥ ከሚገኝ የቆዳ እንክብካቤ ማሠልጠኛ ተቋም ትምህርት በመውሰድ እውቅና አግኝታለች። ወደፊትም በተፈጥሯዊ ግብዓት የምታዘጋጃቸውን የቆዳ መንከባከቢያ ምርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቁ ለማድረግ እንደምትሠራም እንዲሁም የቆዳ መንከባከቢያ ማዕከል ለመክፈት ማቀዷን ጠቁማለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የዋጋ ውድነት የትምህርት ጥራት ያመጣ ይሆን?

**ዋስልኝ አየለ**

ወቅቱ ተማሪዎች የ2016 ዓ.ም የትምህርት ዓመት ጨርሰው ቀጣዩን የ2017 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ለቀጣዩ ክፍል የሚመዘገቡበት ነው። ታዲያ በዚህ የምዝገባ ወቅት በብዙ መንደሮች እየተሰማ የሚገኘው የክፍያ ነገር ነው። እንደሚታወቀው የክፍያ መጨመር በየዓመቱ በሐምሌና ነሐሴ ወር አጀንዳ ነው። የአንዳንድ ትምህርት ቤቶች ዓመታዊ ክፍያ እስከ አንድ ሚሊዮን የሚደርስ መሆኑ አነጋጋሪ ሆኖ እንደነበር አይተናል።

እንግዲህ እዚህ ትምህርት ቤት የሚያስተምር አቅም ያለው ሀብታም ስለሆነ ለከፋዮች አያስጨንቃቸውም እንበል! ዋናው ጥያቄ ግን ያለው ሀገራዊ ፋይዳ ምንድነው? ከዚህ ትምህርት ቤት የሚወጡ ልጆች ምን የተለየ ነገር ያገኙ ይሆን? ቅጥ ያጣ ቅንጦትና ምቾት በበዛ ቁጥር አካባቢያቸውን የመመርመርና የማወቅ ዝንባሌያቸው አይቀንስም ወይ? የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ እና አካባቢውን ያላወቀ ትውልድ ለሀገሩ ምን አይነት ችግር ፈቺ ምርምር ይሠራ ይሆን?

ምናልባት ይሄ የጥቂት ትምህርት ቤቶች (ምናልባትም የአንድ ትምህርት ቤት ብቻ) ሊሆን ይችላል። የዋጋ ውድነት እና ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች ግን ተደጋግመው ሲነገሩና ሲታዩ የቆዩ ናቸው።

እንደምናየውም፣ እንደምንሰማውም፤ የግል ትምህርት ቤት ተመራጭ ነው የሚባልበት ምክንያት ለትምህርት ጥራት ተብሎ ነው (ከግል ትምህርት ቤት የወጣ ተመራማሪ ባንሰማም)።

የግል ትምህርት ቤት ለሀብታም ልጆች የሆነበት ምክንያት ደግሞ ከመክፈል አቅም ጋር ተያይዞ ነው። ድሃ ወላጅ ለግል ትምህርት ቤት የሚሆን የመክፈል አቅም ስለሌለው የመንግሥት ትምህርት ቤት ያስገባል። ጉዳዩ ከክፍያ ጋር መሆኑ ነው ነገሩን የፉክክር ያደረገው። የሀብታምና የባለሥልጣን ልጆች ለስማቸው ክብር ሲባልም ቢሆን የግል ትምህርት ቤት ይገባሉ ማለት ነው።

እኔ ያልታየኝና ያልገባኝ የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ‹‹አለ›› የተባለው የትምህርት ጥራት ነው። ምናልባት የተማርኩት የመንግሥት ትምህርት ቤት ስለሆነ የግሉን ስለማላውቀው ይሆናል። ለጊዜው ወላጅ ስላልሆንኩ ልጅ በማስተማርም በቅርበት አላየሁትም። ይሄ ማለት ግን ስለግል ትምህርት ቤቶች ምንም አላውቅም ማለት አይደለም። የሙያዬም ባሕሪ ነውና ተደጋጋሚ ሥራዎችን ሠርቻለሁ። ብዙ ነገሮችን ታዝቤያለሁ። በቅርበት ከማውቃቸው ጓደኞቼ ብዙ ገጠመኝ አስተውያለሁ። በትምህርት ቤቶች እየገባሁም ለማስተዋል ችያለሁ።

ለማንም ሰው ግልጽ ከሆነው ስያሜያቸው ልጀምር። የግል ትምህርት ቤት ሆኖ ሀገራዊ ስያሜ ያለው ብዙም አላጋጠመኝም። እንዲያውም የአንዳንዶቹ ቃሉን እንኳን ለመጥራት ማስታወሻ ለመያዝ የሚያስገድዱ ናቸው። ትርጉማቸውን ለማወቅም የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት ወይም የኢንተርኔት መረብን መበርበር የሚያስገድዱ ናቸው። የሚገኘው ትርጉም አንድ የውጭ ሀገር ታሪክ ይነግረናል። ቃሉ ብቻ ሳይሆን ሀሳቡና ክስተቱ ራሱ የውጭ ይሆናል።

በሀገር ባለውለታዎች፣ በሀገር ውስጥ ቋንቋ፣ በሀገር ውስጥ ታሪክ፣ ሀገር ውስጥ በተከሰተ መልካም ክስተት ተሰይመው የሚታየው የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ላይ ነው። የትምህርት ቤቱ ስም ራሱን ችሎ አንድ ነገር ያስተምራል። እቴጌ መነንም ሆነ የካቲት 12 የኢትዮጵያ ታሪክ እና የኢትዮጵያ ሰዎች ናቸው። ምኒልክ ትምህርት ቤትም ሆነ በላይ ዘለቀ ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ መሪዎችና አርበኞች ናቸው። ኮከበ ጽባህም ሆነ ምሥራቅ ጎህ ኢትዮጵያዊ ስያሜ ያላቸው ናቸው።

እነዚህ ስያሜዎች ቀላልና ተራ ነገር አይደሉም። ለታዳጊ ሕጻናትና ልጆች ብዙ ነገር እያሳወቁ ነው። በየትኛውም አጋጣሚ የትምህርት ቤቶች ስም ሲጠራ የባለታሪኮች ስም እየታወሰነው። አፌ ላይ የመጡትን ጠቀስኩ እንጂ የብዙ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ስያሜ ሀገራዊ ስም ያለው ነው። እንግዲህ አንዱ የታዘብኩት ነገር ይሄ የስያሜ ልዩነት ነው። ኢትዮጵያዊ ለሆኑ ልጆች፣ አድገው ሀገራቸውን ለሚያገለግሉ ልጆች የግል ትምህርት ቤት በሀገራዊ ስያሜ ቢሰየም ምን ችግር አለው? ወይስ ውጭ ሀገር ካሉ የስያሜው ባለቤቶችና ባለታሪኮች በማስታወቂያ መልክ የሚያገኙት ጥቅም አለ ይሆን?

ሌላው የግል ትምህርት ቤቶች ላይ በሰፊው የሚነሳው ሐሜት ትኩረታቸው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ላይ መሆኑ ነው። ምንም ችግር የለውም! ነገሮችን ለመረዳት፣ ዓለም አቀፍ ሰው ለመሆን እንግሊዘኛ ወሳኝ ነው። ብዙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የእንግሊዘኛ ችሎታ የሚጠይቁ ናቸው። እንግሊዘኛ ፈጣን መሆን የማያከራክር ጥቅም አለው፤ እንዲያውም በዚህ ዘመን ግዴታ ነው። ቋንቋ የኢንተርኔት ቋንቋ ነው።

ችግሩ ግን እንግሊዘኛ ብቻውን ዕውቀት ነው ወይ? የሚለው ነው! የቋንቋ ጥቅም ለመግባባት ነው። እንግሊዘኛ ማወቅ ብቻውን የፊዚክስ ተመራማሪ አያደርግም። የኬሚስትሪ ሊቅ አያደርግም። የተፈጥሮን ምሥጢር ለመመርመር ሀገርኛ ነገሮችን ማወቅ የግድ ይላል። ‹‹አማርኛ መናገርና ድንጋይ መወርወር ያስቀጣል›› በማለት የአገር ውስጥ ቋንቋን መጣል የትም አያደርስም።

ምናልባት ልጆቹ ትምህርት ሲጨርሱ ከአገር ውጭ እንዲሠሩ ይሆን? ለሀገራቸው እንዲያገለግሉ ከሆነ የሀገሩን ቋንቋና ባሕል አራግፎ የጣለ ትውልድ አገር ሊረከብ አይችልም። ለምሳሌ የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪ የሚሆን ከሆነ፤ ወይራ፣ ጽድ፣ ዋንዛ፣ እሬት፣ ፌጦ...... የመሳሰሉ አገር በቀል ሀብቶችን ማወቅ ነበረበት። የማኅበራዊ ሳይንስ ተማሪ የሚሆን ከሆነ፤ ዓድዋን፣ የገዳሥርዓትን፣ ሸምግልናን፣ አሸንዳን፣ ጨምበላላን ማወቅ አለበት። እነዚህን ነገሮች የሚያውቀው ከአካባቢው ሰዎች ነው። ከአካባቢው ተረትና ምሳሌዎች ነው። የአካባቢው ተረትና ምሳሌዎች፣ ተረኮች፣ ታሪኮች ደግሞ የተሰነዱት በእንግሊዘኛ ሳይሆን በሀገሩ ቋንቋዎች ነው። ከእነዚህ ነገሮች የራቀ ተማሪ የማያውቃትን ሀገር ነው የሚረከብ ማለት ነው።

እነዚህ ነገሮች የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ላይ በብቃት እየተሰጡ ናቸው ማለቴ አይደለም። እንዲያውም ቢያንስ በእንግሊዘኛው እንኳን የግል ትምህርት ቤቶች ሊሻሉ ይችላሉ። የመንግሥት ትምህርት ቤት በከፍተኛ ሁኔታ የሚሰማው ቅሬታ ግዴለሽነትና ክትትል ማጣት ነው። መምህሩ ከፈለገው ወር ሙሉ ክፍል ላይገባ ይችላል። ክፍል ውስጥ ገብቶም እንደፈለገው ቀልዶ ሊወጣ ይችላል። በዝርክርክነት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ላይ ያለው ውድቀት ይከፋል። ዳሩ ግን ምን ዋጋ አለው! ከፍተኛ ቁጥጥር ቢያደርጉም የግል ትምህርት ቤቶች ልጆችን ከሀገራዊ ነገሮች እያራቋቸው ነው።

ትኩረቴን የግል ትምህርት ቤቶች ላይ ያደረኩበት ምክንያት የጥራት ማሳያ ናቸው ሲባል ስለምሰማ ነው። የትኛው ምጡቅ ተመራማሪ እንደወጣ ስላልሰማሁ ነው። እንግሊዘኛ ላይ መራቀቅ ብቻውን ተመራማሪና የፈጠራ ሰው ሊያደርግ ስለማይችል ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የሀብታምና የባለሥልጣናት ልጆች ብቻ መሆኑ ነው። የሀብታምነት መለያው ጎበዝና ተመራማሪ ተማሪ ከመፍጠር ይልቅ የትምህርት ቤቱ ስም ብቻ መሆኑ ነው። የመንግሥት ባለሥልጣን የመንግሥትን ብቃት እያቆለጳጰሰ ልጁን የሚያስተምር ግን የግል ትምህርት ቤት ነው። በየደረሰበት ግን የመንግሥትን የትምህርት ጥራት ያወድሳል። ይሄ ባለሥልጣን የመንግሥትን የትምህርት ጥራት አያምንበትም ማለት ነው፤ ወይም ደግሞ የግል ትምህርት ቤት ብቻ የሚያስተምር ለስሙ ክብር ብቻ ነው ማለት ነው።

የግል ትምህርት ቤቶች ልዩነታችሁን በፈጠራችኋቸው ልጆች እውቀት አሳዩን! የዋጋ ውድነት ብቻውን የትምህርት ጥራት አያመጣም!

# ዓለም አቀፍ





## በዶናልድ ትራምፕ ላይ የተኮሰው ሰው ቀደም ብሎ ድሮን አብርሮ ነበር ተባለ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በዶናልድ ትራምፕ ላይ የተኮሰው ሰው ቀደም ብሎ ድሮን አብርሮ ነበር ተባለ፡፡

የፊታችን ህዳር ወር ላይ በሚካሄደው ሪፐብሊካን ፓርቲን ወክለው ለፕሬዚዳንትነት የሚወዳደሩት ዶናልድ ትራምፕ ባሳለፍነው ቅዳሜ የምርጫ ቅስቀሳ በማድረግ ላይ እያሉ በተተኮሰባቸው ጥይት ቆስለው ወደ ህክምና መግባታቸው ይታወሳል።

ለጥቂት ከሞት የተረፉት ዶናልድ ትራምፕ በፔንሲልቫኒያ ግዛት ለደጋፊዎቻቸው ንግግር በማድረግ ላይ ሳሉ ነበር ማቲው ክሩክስ በተሰኘ የ20 ዓመት ወጣት በጥይት የቆሰሉት።

ማቲው ክሩክስ በ130 ሜትር ርቀት ላይ ሆኖ ስናይፐር በተሰኘ የጦር መሳሪያ ዶናልድ ትራምፕን ተኩሶ አቁስሏቸዋል፡፡

የሀገሪቱ ሚስጢራዊ የደህንነት ተቋም ሠራተኞች ወዲያውኑ በወሰዱት የአጸፋ ርምጃ ማቲው የተገደለ ሲሆን ጉዳዩ አሁንም በአሜሪካ እና በመላው ዓለም ትኩረት እንደሳበ ይገኛል።

ቢቢሲ የአሜሪካ ብዙሃን መገናኛዎችን ዋቢ አድርጎ እንደዘገበው ከሆነ ማቲው ክሩክስ ዶናልድ ትራምፕ ንግግር በሚያደርጉበት ቦታ ለይ አስቀድሞ ድሮን አብርሮ ነበር ተብሏል፡፡

ተጠርጣሪው ድሮን ያበረረው ግድያውን ለማሳካት ስለ ሥፍራው በቂ መረጃ ለማግኘት በሚል ሊሆን እንደሚችል በዘገባው ላይ ተጠቅሷል፡፡

ስለ ዶናልድ ትራምፕ የግድያ ሙከራ በየጊዜው አዳዲስ መረጃዎች እየወጡ ሲሆን ከቀናት በፊት የማቲው አባት ልጃቸው የተለየ ባህሪ ማሳየቱን ተከትሎ ፖሊስ ክትትል እንዲያደርግ ከክስተቱ በፊት ሪፖርት አድርገው እንደነበር መገለጹ ይታወሳል።

ከዚህ በተጨማሪም ለዶናልድ ትራምፕ ድጋፍ ለማድረግ ወደ መድረኩ የመጡ ሰዎች ወጣቱ የጦር መሣሪያ ይዞ ማየታቸውን እና ሁኔታውን ወዲያውኑ ለፖሊስ አሳውቀው እንደነበር ተገልጿል።

ይህን ተከትሎም የሀገሪቱ ሚስጢራዊ ደህንነት ጥበቃ ክፍል ሃላፊ እና የአሜሪካ የሀገር ውስጥ ደህንነት ሃላፊ ሃላፊነታቸውን አልተወጡም በሚል ሥልጣን እንዲለቁ ግፊት እየተደረገባቸው ይገኛል ተብሏል።

## ኢራን በሁለት ሳምንት ውስጥ የኑክሌር ቦምብ ግብዓት እንደምታሟላ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር



ኢራን በሁለት ሳምንት ውስጥ የኑክሌር ቦምብ ግብዓት እንደምታሟላ ተገለጸ፡፡

ከምዕራባውያን ጋር ሆድና ጀርባ የሆነችው ኢራን በመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ዋነኛ የስጋት ምንጭ መሆኗን አሜሪካ አስታውቃለች፡፡

የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አንቶኒ ብሊንከን በኮሎራዶ በተካሄደ የጸጥታ እና ደህንነት ጉባዔ ላይ ተገኝተው እንዳሉት፤ ኢራን በአንድ አልያም በሁለት ሳምንት ውስጥ የኑክሌር ቦምብ መስራት የሚያስችላትን ግብዓት ታሟላለች ብለዋል፡፡

ሚኒስትሩ አስፐን በተሰኘው ዓለም አቀፍ የደህንነት ጉባዔ ላይ ባደረጉት ንግግር አሁን ያለንበት ቦታ ትክክለኛው አይደለም ያሉ ሲሆን፤ ስለ ኢራን ኑክሌር ጉዳይ መሰል አስተያየት ሲሰጡ ይህ የመጀመሪያቸው ነው ተብሏል፡፡

ኢራን እስካሁን የኑክሌር ቦምብ አልታጠቀችም የሚሉት ብሊንከን ጉዳዩን በጥንቃቄ መከታተል ይኖርብናል ሲሉም ተናግረዋል ሲል ሲኤንኤን ዘግቧል፡፡

የአሜሪካ ፖሊሲ ኢራን ኑክሌር ቦምብ እንዳትታጠቅ ነው ያሉት ብሊንከን እስካሁን ኢራን እቅዷን እንዳታሳካ ዲፕሎማሲን ስትከተል መቆየቷንም ተናግረዋል፡፡

ከአንድ ዓመት በፊት የአሜሪካ ከፍተኛ የመከላከያ አመራር ኢራን እስካሁን በ12 ቀናት ውስጥ አንድ የኑክሌር ቦምብ መሥራት የሚያስችል ግብዓት መሰብሰቧን ተናግረው ነበር፡፡

የፕሬዚዳንት ባይደን አስተዳደር ከኢራን ጋር በሶስተኛ ወገን በኩል ስትደራደር የቆየ ሲሆን በተለይም በፈረንጆቹ 2018 ላይ በዶናልድ ትራምፕ አስተዳደር ዘመን የተሰረዘው የኢራን ኑክሌር ስምምነትን ዳግም ለማስጀመር ሲወያዩ እንደቆዩም በዘገባው ላይ ተጠቅሷል፡፡

ይሁንና በ2022 በዓለም አቀፉ አቶሚክ ሃይል ምርመራ ወቅት ኢራን በድብቅ ዩራኒየም እያበለጸገች መሆኗን የሚያሳይ ፍንጭ ማግኘቱን ተከትሎ የሁለትዮሽ ውይይቱ ተቋርጧል ተብሏል፡፡

የእስራኤል- ሐማስ ጦርነት ላይ አሜሪካ በቀጥታ መሳተፏን ተከትሎ በኢራን ይደገፋሉ የሚባሉ ታጣቂዎች በመካከለኛው ምስራቅ የሚገኙ የአሜሪካ ወታደራዊ ማዘዣዎችን ኢላማ አድርገዋል፡፡

የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ
ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ‹‹ደራርቱ ቱሉ የሥልጠናና ምርምር ኢንስቲትዩት የመሮጫ መም ችግርን ይቀርፋል››


-አትሌት ቀነኒሳ በቀለ

ዓለማየሁ ግዛው

በኦሮሚያ ክልል መንግሥት በሱሉልታ ተገንብቶ ባለፈው ሐሙስ ለምርቃት የበቃው ደራርቱ ቱሉ የስፖርት ማሠልጠኛ እና ምርምር አካዳሚ በኢትዮጵያ ስፖርት ዘርፍ የሚታየውን ክፍተት በተለያየ መንገድ ይቀርፋል ተብሎ ይጠበቃል። ከነዚህም መካከል ከማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ ከተተኪ ስፖርተኞች፣ ስፖርቱን በጥናትና ምርምር በመደገፍ፣ ስፖርት ቱሪዝምን ከማሳደግ እና የገቢ ምንጭ ከማድረግ አንጻር የሚታዩት ችግሮች ይጠቀሳሉ፡፡

ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ በምርቃት ሥነ ሥርዓቱ ላይ በተገኘበት ወቅት፤ የአካዳሚው መገንባት ለክልሉ እንዲሁም ለሀገር ስፖርት ብዙ የሚያቃልላቸው ችግሮች እንዳሉ ማስተዋሉን ገልጿል። ጀግናዋና የመጀመሪያዋ ጥቁር ሴት የኦሊምፒክ 10ሺ ሜትር ባለድል አትሌት ደራርቱ ቱሉ የተሰየመው አካዳሚው፤ የኦሊምፒክን እና የፊፋን ደረጃ በማሟላት በዘመናዊ ሁኔታ ተገንብቷል። አካዳሚው በ16 ስፖርቶች 800 ሠልጣኞችን የመቀበል አቅም ያለው ሲሆን፤ የመሮጫ መም፣ የእግር ኳስ፣ የእጅ ኳስ፣ የመረብ ኳስ እና የቅርጫት ኳስ ሜዳን አካቷል፡፡

ይኸውም በተጠቀሱት ስፖርቶች ወጣትና ተተኪ ስፖርተኞችን ከማፍራት በተጨማሪ በኢትዮጵያ የሚታየውን የስፖርት ማዘውተሪያ ችግር በማቃለል የድርሻውን ይወጣል። ኢትዮጵያ በምትወዳደርባቸው ዓለም አቀፍና አሕጉር አቀፍ የስፖርት ውድድሮች የእግር ኳስ ሜዳ እና የመሮጫ መም እጦት ለብሔራዊ ቡድኖች ዝግጅት ፈታኝ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል።ቀናት ብቻ ለቀሩት የፓሪስ ኦሊምፒክ ዝግጅት ላይ የሚገኘው ብሔራዊ ቡድንም ከዚሁ ጋር በተያያዘ እየተፈተነ መሆኑን በማሳያነት ማንሳት ይቻላል።



አካዳሚው በ30 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈና የቤት ውስጥ፣ የመም እና የሜዳ ላይ ስፖርቶችን ማካሄድ የሚችል ነው፣

በመሆኑም የአካዳሚው መገንባት ችግሩን ከመቅረፍ አልፎ ኢትዮጵያ አሕጉር አቀፍ ውድድሮችን እንድታዘጋጅም ጭምር ዕድል እንደሚፈጥር ይታመናል። የኦሊምፒክና የዓለም ሻምፒዮና ባለድሉ አትሌት ቀነኒሳ በቀለም ትልቅና ዘመናዊ የሆነ የስፖርት አካዳሚ መገንባቱ ለአትሌቲክስ ከፍተኛ አበርክቶ እንዳለው አስተያየቱን ይሰጣል። በዚህ ደረጃ ይሠራል ብሎ ያልጠበቀው አካዳሚው ሱሉልታ ላይ መገንባቱ የሚያስገኘው ጥቅም ከፍተኛ በመሆኑ አዲሱ ትውልድ በአግባቡ ሊጠቀምበት ይገባል። ተቋሙ እንደ ሀገርም አስፈላጊ በመሆኑ ሠልጣኞች ከረዳት ኮሚሽነር አትሌት ደራርቱ ቱሉ ታሪክ ጋር ተያይዞ በሞራልና በመነሳሳት እንዲሠለጥኑም ያደርጋቸዋል።

እንደ ቀነኒሳ አስተያየት፣ በአካዳሚው የተሠራው ጥራቱን የጠበቀ የመሮጫ መም (ትራክ) ቀነኒሳ በአካባቢው ካስገነባውና በብቸኝነት የሀገር ውስጥና የተለያዩ ዓለም መጥተው ለሚሠሩ አትሌቶች በሚሰጠው አገልግሎት ብዛት ለተጎዳው የመሮጫ መም ጫና ይቀንሳል።አትሌቶች እንደ አማራጭ የሚሠሩበት በማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረውም ጀግናው አትሌት ያስረዳል። በተጨማሪም በርካታ አትሌቶች በስፍራው ባለው ተስማሚ አየር ዝግጅት በማድረግ በሀገር ደረጃ ውጤታማ ለመሆን ያስችላል። ወጣት ሠልጣኞች ከአትሌት ደራርቱ ቱሉ ድል አድራጊነት ልምድ በመውሰድ እንዲጠቀሙበትና ታሪኳን መልሶ እንደሚጽፉም ይታመናል። ከዚህ በፊት የተሠራውን ታሪክ በምርምር ለመደገፍና ተተኪውን ትውልድ በስፖርት ጠንካራ አድርጎ ለማሠልጠንም የአጋጣሚው የሚጫወተው ሚና የጎላ ይሆናል።

የክልሉ ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ በበኩላቸው፣ አካዳሚውን መርቀው በከፈቱበት ወቅት ካነሱት ዋና ዋና ነጥቦች መካከል የቀድሞቹ ውጤታማ አትሌቶች በየጫካውና ገደላገደሉ ልምምድ እየሠሩ ሀገርን ማስጠራት መቻላቸውን ነው። አሁን ያሉት አትሌቶች ደግሞ በአካዳሚ ውስጥ በእውቀት እና በሥልጠና በመታገዝ ውጤታማ ለመሆን እድል ያገኛሉ።

በኦሮሚያ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የስፖርት ማዘውተሪያና ፋሲሊቲ ዳይሬክተር አቶ ግርማዬ ለታ፤ አካዳሚው የቀድሞ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ በሁሉም ክልሎች አንድ ደረጃውን የጠበቀ አካዳሚ እንዲገነባ በሰጡት መመሪያ መሠረት መጀመሩን ያስታውሳሉ። በዚህም ጨረታ ወጥቶ በ2008 ዓም ከአሸናፊው ኮንትራክተር ጋር ውል ታስሮ ወደ ሥራ ተገብቷል። የፕሮጀክቱ ሥራ ከተጀመረ በኋላም በበርካታ ችግሮች ውስጥ አልፏል፤ መጀመሪያ 700 ሚሊዮን ብር በጀት ተይዞ ነበር። ይሁን እንጂ ሥራው በተለያዩ ችግሮች በመጓተቱና በየወቅቱ የሚታየው የግንባታ እቃዎች ዋጋ መናር ታክሎበት ከ1ነጥብ5 ቢሊዮን ብር በላይ ፈጅቶ ተጠናቋል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማካይነት የአምስት ስፖርቶች የሥልጠና ማኑዋልም ተዘጋጅቷል፡፡

አካዳሚው በ30 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈና የቤት ውስጥ፣ የመም እና የሜዳ ላይ ስፖርቶችን ማካሄድ በሚያስችል ሁኔታ እንደተሰራም ያስረዳሉ። ጂምናዝየሙም ደረጃውን ጠብቆ የተገነባና ጥራታቸውን በጠበቁ ቁሳቁሶች ከጣሊያን ተገዝተው ሊሟሉለት ችለዋል። ስፍራው የተመቸ የአየር ንብረትን በመያዙ የውጪ ሃገር አትሌቶችን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ በማድረግ ለሀገር ገጽታና ስፖርት ቱሪዝም ትልቅ አበርክቶ ይኖረዋል። በተጨማሪም አካዳሚው የተሟላ በመሆኑ አሕጉርና ዓለም አቀፍ ስፖርት ጉባኤዎችን ማካሄድ ይቻላል፡፡